የደም ባንኳ መስፋት በሽታ (ማቆር)
ገጽ 14

ገዢው አልረፈደም!
ገጽ 15

አዲስ ዘመን ቀዳሚ

ቁጥር 360 ነሐሴ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ዋጋ 5.75

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



“የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ አሁን ላይ ፀጥ እንዳለ ባህር ሆኗል”

- አቶ አንዷለም አራጌ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር



ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ ፦ የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ አሁን ላይ ፀጥ እንዳለ ባህር ሆኖ እንደሚታይ ይሁንና በሀገሪቱ ያለው እውነታ ኢትዮጵያዊነት ጠፍቷል፤ ዘረኝነት ነግሷል በሚባል ደረጃ የሚሰላ እንዳልሆነ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር አቶ አንዷለም አራጌ አመለከቱ።

የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር አቶ አንዷለም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ አሁን ላይ ፀጥ እንዳለ ባህርና ዝም ብሎ እንደሚፈስ ውሃ ጎልቶ አይሰማም።በሌላ በኩል ደግሞ ጥቂቶች እንደሚረብሽ ሞተር ድምፅ እያሰሙ በባህሩ ላይ የሚሄዱ ጀልባዎችን መስለው በመታየት ጩኸታቸው የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ የአንድነት መንፈስ የሌለ አስመስሎታል።

ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት በየአካባቢው የሚታየው ብሄር ተኮር ግጭት በአገሪቱ አገራዊ አንድን የአገር ፍቅር ስሜት የጠፉ ቢያስመስሉትም ህዝቡ ጉዳቱ የከፋ እንዳይሆን ያደረገው ሁለንተናዊ ጥረት ተቻችሎ የመኖርና ኢትዮጵያዊነት ዛሬም በሁሉም ዜጋ ልብ

የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል

ኤጀንሲው ለአውደ ዓመቱ የምግብ ፍጆታዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ላይ ነው
ገጽ 2

የዘመን አቆጣጠራችን ሳይንስ እና ጥበብ
ገጽ 12

በአራት አካል ጉዳተኛ ልጆች የተፈተነ የቤተሰብ ሕይወት
ገጽ 16

NG ጋዜጦችና መጽሔቶች ሽያጭና አከፋፋይ

በተጨማሪም ያገለገሉ፦
- ጋዜጦችን
- ወረቀቶችን
- ቦክስ ፋይል
- ካርትሬጅ
- ብረታ ብረቶችን እንገዛለን።



0933 91 76 91/0913 44 89 00
0922 87 18 52
አድራሻ
ቁ.1 አራት ኪሎ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
– 0111 26 26 27 – 0922 11 53 24/26
– 0111 26 26 28 – 0922 72 74 48/49
– 0111 26 26 29 – 0922 72 38 70
– 0111 26 26 30 – 0922 72 38 72
ፋክስ፦ 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

ፓርቲዎች ፌዴሬሽን ምክር ቤት የትግራይ ክልል ምርጫን በሚመለከት ጠንካራ ውሳኔ እንዲያስተላልፍ ጠየቁ

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ፦ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ዛሬ በሚያካሂደው አስቸኳይ ስብሰባ የትግራይ ክልል ምርጫን በሚመለከት ጠንካራ ውሳኔ እንዲያስተላልፍ የተለያዩ ፓርቲዎች ጥሪ አቀረቡ::

የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፤ ህብር ኢትዮጵያና ኢዜማ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ የፌዴሬሽን

ፓርቲዎች ፌዴሬሽን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የትግራይ ፖለቲከኞች በክልሉ ያለው አፈናና እንግልት ተጠናክሮ መቀጠሉ አሳስቦናል አሉ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፦ በትግራይ ሊካሄድ ለታቀደው ክልላዊ ምርጫ አስመልክቶ ህወሃት ህዝቡ ላይ እያደረሰ ያለው አፈና እና እንግልት ተጠናክሮ መቀጠሉን እንዳሳሰባቸው በትግራይ ክልል የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ አመራሮች አመለከቱ።

የራያ ራዩማ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ አግዘው ህዳሩ እና የፈንቅል የወጣቶች እንቅስቃሴ

የትግራይ ፖለቲከኞች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ADAMA STEEL FACTORY



0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565





ኤጀንሲው ለአውደ ዓመቱ የምግብ ፍጆታዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ላይ ነው

መልካም ስራ አፈወርቅ

አዲስ አበባ - መጪውን የአዲስ ዓመት በአል አስመልክቶ አስፈላጊ የምግብ ፍጆታዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ማድረግ መጀመሩን የአዲስ አበባ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ግዛቸው ዓሊ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፣ የምግብ ፍጆታዎቹ ከዛሬ ጀምሮ በመጪዎቹ የበአል መዳረሻ ቀናት በከተማዋ በሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራት ተደራሽ ይሆናሉ ::

በአዲስ አበባ ከተማ 148 ህብረት ስራ ማህበራት መኖራቸውን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ ፣ የምግብ ፍጆታ አቅርቦቱ መዳረስ የሚጀምረውም በእነዚህ ተቋማትና በአስር ዩኒየኖች አማካኝነት መሆኑን ተናግረዋል።

ለበአሉ አስፈላጊ የሚባሉ የምግብ ፍጆታዎችን ለማቅረብ በተደረገው ጥረት የእርድ በሬዎችን ጨምሮ ዶሮና ዕንቁላል፣ዓይብና ቅቤ፣ሽንኩርት፣ ዘይትና ዱቄት በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ እንደሚቀርብ አስታውቀዋል::

እንደዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የአዲስ ዓመትን በአል አስመልክቶ ወደ ከተማዋ እየገቡ ያሉት የምግብ ፍጆታዎች ከተለያዩ ክልሎች የተሰባሰቡ ናቸው ። በዋንኛነትም ከሀሮማያና አፍረንቀሎ ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲዎች ጋር ትስስር በመፍጠር የተገኙ ናቸው::

የምግብ ፍጆታዎቹን አስመልክቶ ለሚኖረው እንቅስቃሴ ምንም አይነት የአቅርቦት ችግር እንደማይፈጠር የተናገሩት አቶ ግዛቸው፤ ፍጆታዎቹ በተመጣጣኝ ዋጋ ከመቅረባቸው በዘለለ ጥራትና ደረጃቸው የተረጋገጠ መሆኑን ገልጸዋል::

በአሁኑ ጊዜ አርባ ብርና ከዛም በላይ እየተሸጠ ያለውን የሽንኩርት ዋጋ በማረጋጋት በኪሎ አስራ ስምንት ብር ለማቅረብ መታሰቡን የጠቀሱት አቶ ግዛቸው፣ ቀደም ሲል በየመደብሩ በሊትር እስከ 420 ብር ሲሸጥ የቆየውን የምግብ ዘይትም በየማህበራቱ ሱቆቹ በብር በ285 እንደቀረበ ተናግረዋል::

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ መንግስት በተለይ የምግብ ዘይትን በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ለማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል ። ምርቶቹን ከውጭ አገራት የሚያስመጡ ነጋዴዎች ከታክስ ውጭ እንዲያስገቡ መፍቀዱም ገበያውን ለማረጋጋት አስተዋጽኦ አበርክቷል::

በአሉ ሲቃረብ የገበረው ፍላጎትና ቁጥር በእጥፍ ከመጨመሩ ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን መጨናነቅ ለመቀነስ፣ በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች የማስተባበር ስራ እንደሚከወን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፣ ግብይቱን ለማቀላጠፍ ተጨማሪ የሰው ሀይል ለመጠቀም መታሰቡን ተናግረዋል ::

የአዲስ ዓመትን ገበያ ለማረጋጋት በሚኖረው ሂደት ምርቶቹን ከሸማቾች ሱቅ በቅናሽ በመግዛትና በማከማቸት በትርፍ ለመሸጥ የሚያስቡ ነጋዴዎች እንደሚኖሩ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፣ ይህን ህገወጥ ተግባር በሚፈጽሙ ግለሰቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንደሚደረግ አመልክተዋል::

ከምርቶቹ ተመጣጣኝ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ፍጆታዎቹን ለመሸጥና ለመግዛት የድለላ ስራ በሚያከናውኑ ህገወጦች ላይ እርምጃዎች እንደሚወሰዱ አሳስበዋል::

ህብረተሰቡ ይህን መሰል ህገወጥ ተግባር በሚፈጽሙ ላይ ጥቆማ በማድረግ ገበያውን በትርፍ ከሚይዙ ነጋዴዎች ሊጠበቅ ይገባል ያሉት አቶ ግዛቸው፣ ድርጊቱን ለመቆጣጠርም የሚመለከታቸው የጸጥታ አካላትና ኤጀንሲው የተለየ ትኩረት ሰጥተው እንደሚንቀሳቀሱ አስታውቀዋል::

አራት አመት ተኩል ዕንቅልፍ ያልተኛው ኢትዮጵያዊ የዓለምን ክብረወሰን ለመስበር አቅዷል

ገትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ:- እንቅልፍ በአይኑ ከዞረ አራት አመት ተኩል እንደሆነው የሚናገረው አቶ ቁምላቸው አሰፋ ጉዳዩ እንግዳ ነገር በመሆኑ የጤና እክል እየፈጠረበት ቢገኝም ለረጅም ጊዜ እንቅልፍ ያለመተኛትን የአለም ክብረወሰን የመስበር እድል እንዳለው ገልጿል።

በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ዳውሮ ዞን ኢሰራ ወረዳ ነዋሪ የሆነው አቶ ቁምላቸው አሰፋ ለአዲስ ዘመን እንደገለጸው፤ ከሚያዚያ 18 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ በተፈጠረ አጋጣሚ እንቅልፍ መተኛት አልቻለም። የእንቅልፍ እጦት ቢኖርበትም በምሽት መኝታው ላይ አረፍ ለማለት ሲፈልግ ግን የሰውነት ሙቀቱ እንደሚጨምር እና ጎኑን ውጋት ይሰማዋል። እንግዳ ጉዳዩ ችግር እየፈጠረበት ቢሆንም ግን ለረጅም ጊዜ ያለእንቅልፍ የመቆየት የአለም ክብረወሰን ለመስበር አቅዷል።

ለጉዳዩ መፍትሄ ለማምጣት ከዘመናዊ እስከ ባህላዊ ህክምና እንዲሁም ሐይማኖታዊ መፍትሄዎችን መሞከሩን የሚገልጸው አቶ ቁምላቸው፤ ይሁንና እስካሁን ድረስ እንቅልፍ ማግኘት አለመቻሉን ተናግሯል። በተለያዩ ህክምና ተቋማት በሚሄድበት ወቅት ለጊዜያዊ መፍትሄነት የእንቅልፍ መድሃኒት ቢሰጡትም መድሃኒቶቹ ግን እንቅልፉን ሊመልሱለት አልቻሉም። የጉዳዩ እንግዳ መሆን እና የጤና እክል መፈጠሩ እያሳሰበው መሆኑን ያስረዳል።

በዚህም ምክንያት በመጀመሪያዎቹ የእንቅልፍ እጦት ወራት ለጭንቀት በመጋለጡ እራሱንም ለማጥፋት ጭምር ሙከራ አድርጓል። ይሁንና ከተለያዩ ባለሙያዎች የእንቅልፍ እጦት በእራሱ ችግር አለመሆኑን ምክር ስለተሰጠው ጉዳዩን አምኖ በመቀበል ህይወቱን መቀጠሉን ተናግሯል።

አብዛኛውን ምሽት የእጅ ስልኩን በመነካካት እና ቴሌቪዥን በማየት እንዲሁም የተለያዩ ተግባራትን በመፈጸም እንደሚያሳልፍ የተናገረው አቶ ቁምላቸው፤ እንቅልፍ ባያገኝም የዕለት ተዕለት ስራውን በሰላም ከመከወን እንዳላገደው ገልጿል።

አቶ ቁምላቸው በ2008 ዓ.ም ሚያዚያ ወር ላይ በተዘጋጀ የባህል ፌስቲቫል ላይ የባህል ቡድን በመምራት አሸናፊ እንደነበረ ገልፆ፤ በጊዜው የባህል ቡድኑ አባላት መኝታ ክፍል ሲይዙ እርሱም አንድ ክፍል ውስጥ እንቅልፍ መተኛቱን አስታውሷል። በጊዜው ግን አንድ ወጣት አልጋ ባለማግኘቱ የአካባቢው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ወደእርሱ ደውሎ አልጋ ያላገኘ ወጣት መኖሩን ገልጾ አብሮት እንዲያድር እንዲተባበረው ይጠይቀዋል። እሺታውን የገለጸው አቶ ቁምላቸውም ወጣቱን ተቀብሎ አብሮ ቢተኛም እንቅልፍ ግን ሊወስደው አልቻለም። በዚያን ቀን ከሰው ጋር በመተኛቱ እንቅልፍ ሊወስደው እንዳልቻለ ያሰበው አቶ ቁምላቸው፤ በሌሎች ቀናት በቤቱም ብቻውን ለመተኛት ቢሞክርም እንቅልፍ ሊወስደው እንዳልቻለ አስረድቷል።

ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁት የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ተርሜ ካምፓስ የጤና ሳይንስ መምህር አቶ ውብሸት ጌታቸው እንደገለጹት፤ የግለሰቡን የእንቅልፍ ችግር ለማስወገድ ሲባል በተለያዩ ጊዜያት የእንቅልፍ መድሃኒት እንዲወስድ ተደርጓል። ጉዳዩ የስነልቦና፣ ችግር ወይንም የሱስ ሊሆን እንደሚችል ቢገመትም አቶ ቁምላቸው ግን ጭንቀትም ሆነ ሱስ እንደሌለበት ገልጾ፤ በተለያዩ ሆስፒታሎች መፍትሄ ፍለጋ ዞሯል። ይሁንና ለአራት ዓመታት ተኩል እንቅልፍ ሳያገኝ መኖሩ የባሰ የጤና ችግር ሳያመጣበት ወደውጭ ሀገራት ሄዶ ቢታይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል።

በዳውሮ ዞን ኢሰራ ወረዳ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ጽህፈት ቤት ኃላፊው እና የአቶ ቁምላቸው የቅርብ ጓደኛ አቶ ባደግ ወንድሙ በበኩሉ፤ የጓደኛው እንቅልፍ እጦት ጉዳይ ለማየት አብሮት ሁለት እና ሶስት ቀናት እንደተኛ ገልጿል። ይሁንና አብረው በሚያድሩበት ጊዜ እስከ ሌሊቱ ስምንት እና ዘጠኝ ሰዓት ከቆዩ በኋላ



አቶ ቁምላቸው አሰፋ

እሱ እንቅልፉ መጥቶ ሲተኛ አቶ ቁምላቸው ግን እንቅልፍ መተኛት እንደማይችል ተናግሯል።«እኔንም በተደጋጋሚ ቀስቅሶ አብሬው እንድቆይ ሲጠይቀኝ ነበር» ሲል እማኝነቱን ገልጿል።

አቶ ባደግ እንደገለጸው፤ የአቶ ቁምላቸው የእንቅልፍ እጦት በተለይ ምሽት ላይ የጤና ችግር እያስከተለበት በመሆኑ የተሻለ ህክምና ባለሙያዎች እንዲያዩት ጥረት መደረግ አለበት። በተጨማሪም ችግሮችን ለመልካም አጋጣሚ መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ ቁምላቸው ለረጅም ጊዜ እንቅልፍ ባለመተኛት በሚል ዘርፍ የጊነስ ወርልድ የአለምን ክብረወሰንን የመስበር ትልቅ እድል አለው። በዚህም እራሱን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም የማስተዋወቅ እድሉ ሰፊ በመሆኑ ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል።

ረጅም ጊዜ እንቅልፍ ያለመተኛት የዓለም ክብረወሰን የተያዘው በአሜሪካዊው ራንዲ ጋርነር ሲሆን ። ቀን ከ25 ደቂቃ ያለእንቅልፍ በመቆየት ከ56 ዓመታት በፊት ክብረወሰኑን ይዟል።



መጪው ዓመት በዲፕሎማሲ መስክ ውጤታማ ስራ የሚሰራበት እንደሚሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አስታወቁ

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- መጪው አዲሱ ዓመት ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም ባላት ግንኙነት ውጤታማ የዲፕሎማሲ ስራ የምትሰራበት እንደሚሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አስታወቁ ::መንግስት በሳውዲና በየመን ችግር ውስጥ ያሉ ዜጎችን ወደ አገራቸው ለመመለስ ዝግጅት እያደረገ እንደሚገኝም ተገለጸ::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት በሳምንታዊ መግለጫው ላይ የተገኙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው እንዳስታወቁት፤ መጪው አመት ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም ባላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ውጤታማ ስራ የምትሰራበት ዓመት እንደሚሆን ያላቸውን እርግጠኝነት አሳውቀዋል::

አዲሱ ዓመት ለኢትዮጵያና ለህዝቦቿ ስኬት የሚዘጉበት፣አገራችን ወደ ተሻለ ከፍታ የምትወጣበት፣ በመላው ኢትዮጵያ ሰላም የሚሰፍንበት፣ሁሉም ህዝብ ለልማት እና ለለውጥ በጥሩ መንፈስ የሚንቀሳቀስበት እንደሚሆንም አመልክተዋል።

በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ባሏት ዲፕሎማቶች ውጤታማ ስራ በመስራት አገሪቱ በተሻለ መልኩ ተጠቃሚ የምትሆንበት ዓመት እንደሚሆንም ያላቸውን ምኞት ገልጸዋል::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው፤ በሳዑዲ ችግር ያጋጠማቸውን ዜጎቻችንን ከመስከረም እስከ ጥቅምት መጀመሪያ ወር 2013ዓ.ም ድረስ ወደ አገራቸው ለመመለስ ዝግጅት መደረጉን አመልክተዋል ። በየመን የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ካሉበት ችግር ለማውጣትና ወደ አገራቸው ለመመለስ ከፍተኛ ዝግጅት እየተደረገ እንደሚገኝም ጠቁመዋል::

መንግስት በዜጎች ተኮር ዲፕሎማሲ በተለያዩ አገራት በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙ ወገኖቻችንን ወደ አገራቸው ለመመለስና ባሉበት ችግር እንዳያጋጥማቸው ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ለአብነትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ በተለያዩ አገራት ጉብኝት በሚያደርጉበት ወቅት በአስቸጋሪ ሁኔታና በእስር ቤት የነበሩትን ዜጎች ከእስር በማስፈታት ከእሳቸው ጋር አብረው ወደ አገራቸው እንዲመጡ ማድረጋቸውን አስታውቀዋል::

ከሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ ግንኙነት አንጻር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ከደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንታዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ንሂያል ደንግንሂያል በመሰረተ ልማት በተለይም ሁለቱን አገራት በመንገድ እና በኤሌክትሪክ ለማስተሳሰር በጋራ መስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ መምክራቸውን ጠቁመዋል።

እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምሳደር ሪድዋን ሁሴን ከጀርመንና ከእንግሊዝ አምባሳደሮች ጋር በሁለቱ አገራት በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምሲዎች ደህንነት ዙሪያ ምክክር ማድረጋቸው አገራቱም የኤምባሲዎቹን ደህንነት ለማስጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቃል መግባታቸውን አመልክተዋል።

ለውጡን ተከትሎ በውጭም ይሁን በአገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞን የማቅረብ መብት ቢኖርም የኤምባሲዎችን ስራ የሚያስተጓጉል ተግባር መፈጸም ግን ወንጀል እንደሆነም አስታውቀዋል::

የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነት መጠናከር ለሁለቱ አገሮች ብቻ ሳይሆን ለምስራቅ አፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይጠቅማል ያሉት አምባሳደሩ፤ አሜሪካ በቅርቡ በጊዜያዊነት የወሰደችው 130 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ የመግታት ተግባር የግንኙነታችንን ቁመና አይመጥንም ብለዋል::

የአምባሳደሮች፣ የቆንስላ ጀነራል ጽህፈት ቤቶችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች እያደረጉት ባለው ዓመታዊ ስብሰባ በመደመር እሳቤ ፣በአገር ደህንነትና በአዲሱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዙሪያ ስልጠና መሰጠቱንም አስታውቀዋል::

በተለይ መደመር እሳቤ ዙሪያ የተሰጠው ስልጠና የመደመር ፍልስፍና ሀገራቱን ወደ ሁለንብ ብልጽግና የሚወስድ መሆኑና በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊ እና በውጭ ግንኙነት ዙሪያ ለአምባሳደሮች ትልቅ ግንዛቤ ያስጨበጠ መሆኑን ተናግረዋል።

አዲሱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በጎረቤት አገሮች ላይ ትኩረት ያደረገ፣ ወንድማማችነት እና መግባባትን ያስቀደመ መሆኑን ገልጸው፤ በወታደራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በቴክኖሎጂ በዓለም ላይ የታዩ ለውጦችን ግምት ውስጥ ያስገባ እንደሆነም አስታውቀዋል ።

በኮቪድ 19 ምክንያት በሚኒስቴሩ የቆንስላ ጉዳዮች ክፍል በከፊል ይሰጥ የነበረው የኮንሱላር አገልግሎት ከነሀሴ 29 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ለተገልጋዮች ሙሉ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን አምባሳደር ዲና ተናግረዋል።

በመጨረሻቹ አራት ቀናትም ኤምባሲዎች ሪፖርታቸውን የሚያቀርቡበትና በሚኒስቴሩ 2013 ዓ.ም ዕቅድ ላይ ውይይት የሚደረግ መሆኑን ተናግረዋል፡ ፡አምባሳደሮቹም በስልጠናው ያገኙትን እውቀትና ግንዛቤ ይዘው ለቀጣይ ተልዕኮአቸውን እንደ ስንቅ የሚጠቀሙበት እንደሚሆን አስገንዝበዋል::

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዲጂታል የጉዞ ክፍያ አገልግሎት ጀመረ

ዋስልኝ አየለ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሶልኔት ትራቭል ከተሰኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የአን ላይን የጉዞ ወኪል ጋር በመተባበር ዲጂታል የጉዞ ክፍያ አገልግሎት መጀመሩን አስታወቀ ።

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዲጂታል ባንኪንግ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ የሐንስ ጊሎ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የዲጂታል አገልግሎት የክፍያ አማራጭ ደንበኞች ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል።የዲጂታል ክፍያ መተግበሪያው ከሞባይል ኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ጋር ይተሳሰራል።

እንደ አቶ ዮሐንስ ገለጻ፤ በሶልኔት ትራቭል የተዘጋጀው የጉዞ መተግበሪያ በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር እንዲሰራ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።መተግበሪያው በአምስት ቋንቋዎች የተዘጋጀ ሲሆን አራቱ የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ናቸው።

አማርኛ፣ ኦሮሚኛ፣ ትግርኛ፣ ሶማሊኛ እና እንግሊዘኛ መተግበሪያው የተዘጋጀባቸው ቋንቋዎች መሆናቸውን ያስታወቁት ኃላፊው፤ ደንበኞች በአቅራቢያቸው ከሚገኝ የትኛውም የንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በመሄድ አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ጠቁመዋል ::

በቀጣይ ተቀዳሚ ደንበኞች የበረራ ትኬት በብድር መግዛት የሚችሉበት የአሰራር አማራጭ እንደሚዘረጋ ያመለከቱት አቶ ዮሐንስ፤ አዲሱ የዲጂታል የክፍያ አገልግሎት በረራ የመሰረዝና በድጋሚ ቦታ የማስያዝ አሰራር ያለው መሆኑን አመልክተዋል።

አገልግሎቱ ትኬት ይጠፋብኛል ከሚል ስጋት የሚያድን መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው ፤ ተጓዦች በአንድ አየር መንገድ የቆረጡትን ትኬት በመሰረዝ በወረቀት የታተመ ማረጋገጫ ሳያስፈልግ ወደ ሌላ አየር መንገድ መቀየር እንደሚችሉም አስታውቀዋል።

ከደህንነት አኳያ የትኬት መግዣ የወረቀት ገንዘብ መያዝን እንደሚያስቀር ጠቁመው፤ አገልግሎቱ ዓለም የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ያማከለ በመሆኑ የቱሪዝም ዘርፉን እንደሚያሳድግና የባንኮችን ተቀማጭ ገንዘብ እንደሚጨምር ገልጸዋል።

የጉዞ ጎ/ የሞባይል መተግበሪያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ በሱፈቃድ ጌታቸው እንደገለጹት፤ ዲጂታል የጉዞ ሥርዓቱ የተዘጋጀው በኢትዮጵያውያን ነው፤ ጥገና የሚደረግለትም በኢትዮጵያውያን ነው።የመተግበሪያው የዘመን አቆጣጠሩ እና የሰዓት አቆጣጠር በኢትዮጵያ የሚሰራ መሆኑ አስታውቀዋል።

መተግበሪያው በዘርፉ ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ከማሳየት ባሻገር አገሪቱ የራሷ የዘመንና የሰዓት አቆጣጠር እንዳላት ያሳያል ብለዋል ።መተግበሪያው ለተመረጡት አሥር አገራት ከየትኛውም አገር ወደየትኛውም አገር ለመብረር እንደሚያስችል አመልክተዋል።

ከመተግበሪያው በተጨማሪም 7473 የጥሪ ማዕከል ያለው ሲሆን፤ ለመንገደኛው ከጉዞው ሁለት ሰዓት አስቀድሞ በመደወል መረጃ እንደሚሰጥ ጠቁመዋል ::

«መተግበሪያው ከእንግሊዘኛ ውጪ ባሉ ሌሎች ዓለም አቀፍ ቋንቋዎችም አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል» ያሉት አቶ በሱፈቃድ፤ የሆቴሎች አገልግሎቶችንም በዚሁ መተግበሪያ ማግኘትና ማዘዝ እንደሚቻል አመልክተዋል።

መተግበሪያው አገልግሎት የሚሰጥባቸው አገራት፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኤመሬትስ፣ ሉፍታንዛ፣ ኳታር፣ ተርኪሽ፣ ኬንያ፣ ዱባይ፣ ገልፍ፣ ግብጽ እና ሳውዲ አየር መንገዶች መሆናቸውም በወቅቱ ተገልጿል ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ25 ሚሊዮን በላይ ደንበኞች ያሉት ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ አንድ ሺ 600 ቅርንጫፎችእንዳሉትም ከባንኩ የተገኘ መረጃ ያመለክታል ።

“የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መኖሩን ያመላከተ መሆኑን አስታውቀዋል ።

ለዚህ ደግሞ በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል ተከስቶ የነበረው ችግርና ህዝቡ ያደረገው ትብብር አብነት ተደርጎ ሊጠቀስ እንደሚችል ተናግረዋል።«ኦሮሚያ ላይ አሁን በተፈጠረው ሁኔታ ችግሩን ያቆመው ህዝቡ ነው።ህዝቡን ያቆመው የባጀ፤ የኖረ የኢትዮጵያዊነት ስሜት፤ ተቻችሎ የመኖር እሴቱና ሃይማኖታዊ መርሁ ነው» ብለዋል። ፅንፈኞቹ የሌላ ብሄረሰብ ተወላጆችን በመከታተል ጥቃት ሲያደርሱ ህዝቡ በጉያው በመሸሸግ ለመከላከል ጥረት ማድረጉን አመልክተዋል።

እንደአቶ አንዷለም ገለፃ፤ 1997ዓ.ም ኢትዮጵያዊነት ሞተ ሲባል አገሩን ሞልቶ የቆመው አስቀድሞም ህዝቡ ውስጥ ስሜቱ ስለነበረ ነው።በተጨማሪም እነዶክተር አብይ ሲመረጡ «ሆ» በማለት የወጣው ይህ ህዝብ ስሜት አስቀድሞም በውስጡ ስለነበር ነው።በመሆኑም በአገሪቱ ኢትዮጵያዊነት ጠፍቷል፤ ዘረኝነት ነግሷል የሚባልበት ደረጃ አለመሆኑን ያሳያል::

በአንዳንድ ሰዎች የብሄርተኝነት አስተሳሰብ ጫፍ ደርሷል በሚባልበት በትግራይ ክልል እንኳ ህዝቡ ለአገሩ ያለውን ፍቅር የሚያሳይበትን እድል ባለማግኘቱ እንጂ ሁኔታዎች ቢመቻቹለትና ነፃነቱ ቢጠበቅለት እንዲህ የሚሉትን አካላት እንደሚያሳፍራቸው ያላቸውን እምነት ምክትል ሊቀመንበሩ ገልፀዋል።«ኢትዮጵያዊነቱ ጎልቶ ሲወጣ ለኢትዮጵያዊነት ክብር ሲቆም እናየዋለን።ዛሬ ግን ሕወሓት ስለሚጨፍርና ስለብሄር ብቻ ስለሚያወራ የትግራይ ህዝብ አንደበት ተደርጎ ሊወሰድ አይቻልም» ብለዋል።

እኛ ብናምንበትም፤ ባናምንበትም ህገመንግስቱን ያወጣው ህውሀት ራሱ ነው፤ ሲመራበት ነበር።እሱን አላከበራችሁም እየተባልን ብዙ በደል ደርሶብናል።አሁን ግን መልሶ ራሱ የወለደውን ልጅ ራሱ እየገደለ ነው።ይህ ተገቢ አለመሆኑን ጠቁመዋል ::

“ የትግራይ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ደም የሚያቃባ ነገር ሰራዊት አዘጋጅቶ ማስፈራሪያና ዛቻ ማድረግ አይጠበቅበትም።የሚያሳዝነው ነገር አንዱም የሕወሓት ባለስልጣን ሄዶ አለመሞቱ ነው።በተመሳሳይ የብልፅግና አመራር ሄዶ አይሞትም።የሚሞተው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው።የሚጋደሉት የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው።ይህንን ግፊት እያደረገ ያለው ደግሞ በዋናነት ሕወሓት ነው”ብለዋል ።

ህውሀት እንደሌሎቻችን ታግሶ መጠበቅ ሲኖርበት በተለየ መንገድ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ለመምሰል ሲል ህዝብ ለማጫረስ ጥረት እያደረገ መሆኑን አመልክተው፤ እድሉ በነበረው ጊዜ ዲሞክራሲ በአገሪቱ ማስፈን ሳይችል አሁን ላይ ይህን ለማድረግ መሞከሩ የሚያስተዛዝብ እንደሆነ ገልጸዋል።

ከብልፅግና ሰዎች ጋር በተጋባው አልህ ምክንያት እንዲህ አይነት የተዛባ ነገር መስራት ትክክል ስለመሆኑ ምንም ጥያቄ የለውም ያሉት አቶ አንዷለም ፣ በመንግስት በኩል ባልተገደበ ሁኔታ ነገሩን ዝም ብሎ መተው ትክክል እንዳልሆነ አመልክተዋል። ከፉ ከራው፣ ከዛቻው አልፎ ከመጋረጃ በስተጀርባ ትላልቅ ስራዎች መስራት እንደሚጠበቅበትም አስታውቀዋል ::

በእርግጥ ይህንን ዘመን የሚመጥኑ ከሆነ፣ ለኢትዮጵያ ታላላቅ ሰዎች እንሆናለን ብለው የሚያስቡ ከሆነ ቁጭ ብለው መነጋገር ይጠበቅባቸዋል:: አባቶቻችንም በዚህ መንገድ ነው ያለፉት።ከብዙ ደም መፋሰስና ፍጥጫ መሃል አንዱ ሌላውን ይቅር ብሎ የኖሩበት ዘመን አለም ብለዋል ::

ከአቶ አንዷለም ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ሙሉ ቃል በገጽ 6 ይመልከቱ

ሄራልድ ዘመን ጃንሜዳ...

ገዛዕ ፀር ሙኔፐኒ

ኒኒኒ

አገልግል

የቀጸሜ ሠፈሐቱ



«ጭቃ እየተቀባንም
አገር እንዲረጋጋ
እየሰራን ነው»

- አቶ አንዷለም አራጌ
የኢዜማ ምክትል መሪ

ገጽ 6



የመገናኛ ብዙሃን የክፍያ ጣቢያዎችን ያስተዋወቁ እንስት

ገጽ 13

የደም ባንክ መስፋት በሽታ (ማቆር)

ገጽ 14

በውስጥ ገጾች

ዶሴ	10
ማረፊያ	11
እንዲህም ደኖራል	16

«ጭቃ እየተቀባንም አገር እንዲረጋጋ እየሰራን ነው»

አቶ አንዷለም አራጌ
የኢዜማ ምክትል መሪ

ማህሌት አብዱል



ፎቶ በሔዋን አብርሃ

የተወለዱት በቀድሞው አጠራር ጎንደር ክፍለሀገር ደቡብ ጎንደር ውስጥ በምትገኝ ቀሳ በምትባል አነስተኛ መንደር ውስጥ ነው። እስከ 12 ዓመታቸው ድረስ በዚያችው መንደር በሚገኝ ደብር ቅስና ሲማሩ ቆዩ። በ1977 ዓ.ም ደግሞ አዲስ አበባ ከሚገኙት አያታቸው ቤት በመምጣት ዘመናዊ ትምህርት ቀድሞ መስከረም ሁለት አሁን ደግሞ ባታ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው ተማሩ። የዛሬው የዘመን እንግዳችን ምንም እንኳ ትምህርታቸውን ዘግይተው ቢጀምሩም በቤተክህነት የቆጠሩት ፊደል እገዛ አደረገላቸውና በዓመት ሁለት ገዜ ክፍሉችን በማስፍ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ከዕድሜ እኩያዎቻቸው ጋር ማጠናቀቅ ቻሉ። ኮከበ ፅባህ ትምህርት ቤት ደግሞ ዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ከተማሩ በኋላ ሴንጆሴፍ ትምህርት ቤት በመግባት ቀሪውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ከልጅነታቸው ጀምሮ በአገራቸውና በታሪክ ልዩ ፍቅር ስለነበራቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተውም በታሪክ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አገኙ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች ካውንስል ውስጥ የአካዳሚክና አድሚኒስትሬሽን ሲቀመንበር እንዲሁም ከ12ቱ ሥራ አስፈፃሚ አባላት መካከል አንዱ በመሆንም አገልግለዋል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ማህበረሰብ የሚባል ማህበር ውስጥ ለሁለት ዓመት ፕሬዚዳንት ሆነው ሰርተዋል። ከዩኒቨርሲቲ ከወጡ በኋላ ደግሞ የራሳቸውን ፓርቲ ከጓደኞቻቸው ጋር ለማቋቋም ቢያስቡም ኢዴፓ ተመስርቶ ስለነበር ፓርቲውን ተቀላቀሉ። ፓርቲው በ1997ዓ.ም በቅንጅት ስር እስከሚዋሃድ ድረስ ምክትል ዋና ጸሐፊ ሆነው አገልግለዋል። እንግዳችን አቶ አንዷለም አራጌ ቅንጅት ከምርጫ ጋራ ተያይዞ ከገዢው ፓርቲ በነበረው ግጭት ከታሰሩት አመራሮች አንዱ ሆነው ለሁለት ዓመታት ወህኒ ቆይተዋል።

ከእስር ከተፈቱ በኋላ ግን ፖለቲካን እርግፍ አድርገው ፊታቸውን ወደ ግል ሕይወታቸው ለማዞር ተገደው ቢቆዩም፣ በአገሪቱ የነበረው ጨቋን እና ፀረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመታገል አንድነት ፓርቲን ከሌሎች የትግል አጋሮቻቸው ጋር መሰረቱ። በትግል ውስጥ እንዳሉም ዳግም ለእስር ተዳረጉ። በወህኒ ቤትም የለዕምሮ መቃወስ የሚያደርስ ጫና የተደረገባቸው እኚሁ የፖለቲካ ሰው በአገሪቱ ለውጥ መምጣትን ተከትሎ ከእስር የመፈታት ዕድል አጋጠማቸው። ይህ ብቻ አይደለም፣ ኢዜማን ከመሰረቱት አንኳር ፖለቲከኞች መካከል አንዱ ሆኑ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ፓርቲውን በምክትል መሪነት እያገለገሉ ይገኛሉ። አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከአቶ አንዷለም አራጌ ጋር በግል የፖለቲካ ሕይወታቸውና ወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ቃለምልልስ አድርጓል።

አዲስ ዘመን፡- ወደ ፖለቲካው መስመር የገባህበትን አጋጣሚ አስታውሰንና ውይይታችን እንጀምር?

አቶ አንዷለም፡- የአገር ፍቅር ዕዳ በሚለው መጽሐፌ ላይ በስፋት እንደጠቀስኩት እኔ ያደግሁት ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። ቤተክርስቲያን ውስጥ ደግሞ ሃይማኖታዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ስለሀገርና ስለ ሰላም ይሰበካል። በተለይ ስላሴ ቤተክርቲያን የጀግኖች አባቶቻችን አፅም ያረፈበት በመሆኑ የእነሱን ታሪክ እየዞርኩ እያነበብኩኝ ነው ያደግሁት። እንዲሁም አጎቴ የሰበሰባቸው የኢህአፓ ጊዜ የተፃፉ የፖለቲካ መጻሕፍቶች አነብ ነበር። ትምህርት ቤትም ከፍተኛ ውጤት የማስመዘግበው ፖለቲካና ታሪክ ትምህርቶች ናቸው። በነገራችን ላይ ስድስተኛ ክፍል እያለሁ ነው ወደ ፖለቲካ እንደምገባ የወሰንኩት። ከዚያ ያንን እያሳደኩኝ ነው የመጣሁት። በሌላ በኩል ቤተመንግሥት አጠገብ በማደጌ በራሱ ተፅእኖ እንደፈጠረብኝ አስባለሁ።

አዲስ ዘመን፡- ታዲያ በተቃዋሚ ጎራ ለመሰለፍ የተሰየ ገፊ ምክንያት ነበርዎት?

አቶ አንዷለም፡- ጥሩ ጥያቄ ነው! እንዳልኩሽ ሳድግ ስለኢትዮጵያዊነት፤ ስለሀገር ክብር፤ ስለ ዳር ድንበር፤ ስለባህር በር፤ ስለ ሀገሪቱ ታሪክ እና ገናናነት እንዳውቅ ተደርጌ ነው የተገነባሁት። ኢህአዴግ ሲመጣ ግን ያንን ለዘመናት የተገነባሁበትን ማንነት ናደብኝ። የባህር በር ጉዳይ ታሪክ ሆኖ ቀረ። በተለይ ለታሪክ ዝቅ ያለ ዋጋ እንዲሰጠው መደረጉ ሥርዓቱን መቀበል አቃተኝ። በእርግጥ በወቅቱ ልጅ ስለነበርኩኝ ስለፖሊሲው ጉዳዮች በሚገባ ገብቶኝ ሳይሆን ግን በዋናነት ለሀገር ምሰሶ የሚባሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፤ ታሪኩን ባህሉን ለዚያ የነበረው እይታ ማንነቴን ተፈታተነው። ጥላቻው ከዕለት ዕለት እየጨመረ በመምጣቱ አምርሬ እንድታገለው አደረገኝ። እንደሚታወቀው ደግሞ ኢዴፓ፤ ቅንጅትና አንድነት ፓርቲዎች ውስጥ በነበርኩበት ውስጥ ኢህአዴግን በድፍረት ከሚታገሉት ሰዎች አንዱ ስለነበርኩኝ። በዚህም በድምሩ ለስምንት ዓመት ተኩል ታስሬያለሁኝ።

አዲስ ዘመን፡- ለረጅም ዓመታት እስርቤት ቢያሳልፉም ልክ እንደሴሎች ፖለቲከኞች ያሳሰፉትን ችግር መናገር አይወዱም፤ ስለዚህ የተሰየ ምክንያት ይኖርዎት ይሆን?

አቶ አንዷለም፡- እኔ ስላሳለፍኩት ነገር መናገር የማልፈልገው በሦስት ምክንያቶች ነው። አንደኛው ለዚህች አገር ከእኔ በላይ ብዙ ዋጋ የከፈሉ ሰዎች አሉ። እኔ ያሳለፍኩት ችግር ከእነሱ የሚበልጥ ወይም የሚጋነን ነው ብዬ አላስብም። ብዙ ሰዎች የመጨረሻ የሚባለውን ዋጋ ከፍለዋል። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን በሕይወት ቆይቼ የሰው ፍቅርና ክብር አግኝቼ ዛሬ ታሪክ እየተናገርኩ ነው። በሁለተኛ ውስጤን የሚያሙኝና ላስታውሳቸው የማልፈልጋቸው ነገሮች አሉ። እሱንም ማስታወስና መቀስቀስ ስለማልፈልግ ነው የማልናገረው። በተጨማሪም ደግሞ አሁን ላይ እኔ ስለመቻቻልና ስለፍቅር እንድናወራ እንጂ ያለፈው ዘመን እስረኞች እንድንሆን አልፈልግም። እኔም የእስርቤት ሕይወቴን እያሰብኩ ቀሪ ሕይወቴን እስረኛ ሆኜ ማሳለፍ አልፈልግም። ያለፈውን ነገር ባነሳሁኝ ቁጥር እዚያ ህመም ውስጥ ይመልሰኛል። እንደዚህ ዓይነት ቁስል ውስጥ መቆየት አልፈልግም።

ግን ዞሮ ዞሮ የታሰርኩት በድምሩ ስምንት ዓመት ተኩል ለሚሆን ጊዜ ቢሆንም በተለይ ያለፉት ስድስት ዓመት በጣም ከባድ የሚባል እስር ነው። የአዕምሮ ጤንነቴንም ችግር ውስጥ የሚከት ነበር ማለት እችላለሁኝ። ግን ምንም ማለት አይደለም። ምክንያቱም ነፃነት ዝም ብሎ አይገኝም፤ ብዙዎች ዋጋ ከፍለዋል። ዛሬ ላይ ስማቸው የማይነሳ ነገር ግን የእኛን ግማሽ ዕድሜ ያልኖሩ ወጣቶች ሞተዋል። ስለዚህ እንዲያውም የእኔ መባረክ ነው፤ እግዚአብሔር ትንሿን ነገር ባረከልኝ። አንዳንዴ እንዲያውም ይሰማኛል፤ በእኔ ምክንያት ሌሎች የተከለሉ ይመስለኛል። እኔ በእርግጥ አዕምሮዬን የሚፈታተኑ ነገሮች አጋጥመውኛል። ሊያሳብዱኝም ብዙ ጥረት አድርገዋል። ይሁንና ይሄነው የሚባል አካላዊ ዱላ አልደረሰብኝም። ሌሎቹ ግን የአካልም ሆነ የጭንቅላት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች ተፈፅሞባቸዋል። በአጠቃላይ የእኔ ሊነገር ብዬ ብዙ አላምንም። እንዲያውም ፈጣሪን አመሰግናለሁ።

አዲስ ዘመን፡- ከአንተ ጋር የታሰሩና ተፈተው የነበሩ አንዳንድ ግለሰቦች አሁን በተቃዋሚ ጎራ ተሰልፈው አሁንም እስርቤት ውስጥ የገቡበት አጋጣሚ አስ፤ ይህንን ሲያዩ ስሙ ውስጥ ስሳልመጣ ነው ሰዎቹ በራሳቸው የተሰየ ችግር ስሳስባቸው ነው?

አቶ አንዷለም፡- አየሽ በየምዕራፉ የሰውልጅ እይታ ይለያያል። አንዳንዶቹ ለእኔ ከወንድም በላይ ናቸው። ለምሳሌ እኔ በሰላማዊ ትግል የማምን ሰው ብሆንም የእኔ ታናሽ ወንድም በትጥቅ ትግል ነበር የሚያምነው። ከዚህ ወንድሜ ጋር የአንድ እናት ጡት ጠብተን ብናድግም ግን እሱ በኃይል ትግል ያምን ስለነበር ኤርትራ ሄዶ ሲታገል ሞቶ እዛው ነው የተቀበረው። እናም የአንድ እናት ልጅም ሆነሽ በአስተሳሰብ ልትለያዪ ትቺያለሽ። በሌላ በኩል ግን እኔ እውነቱን ለመናገር በፍርድ ቤት የተያዘ ጉዳይ ስለሆነ ብዙ መናገር አልፈልግም። ደግሞም ይህንን ስሜት አውቀዋለሁ። ታስታውሺ እንደሆነ እኛ እስርቤት ሳለን «አኬልዳማ» የሚል ፊልም ሰርተውብናል። በወቅቱ እኛ መናገር በማንችለበት ሁኔታ ያንን ፊልም በቴሌቪዥን ያሳዩ ነበር። በወቅቱ በአንዳንዶቹ ጋዜጠኞች በጣም አዝን ነበር። ልክ እንደእውነተኛ ታሪክ ለማስመሰል ሲሉ ደምስራቹው እስኪገታተር ነበር የሚያነቡት። በተለይ ወጣቶች ሆነው ከተማሩበት ሥነምግባር ውጪ የሆነ ሥራ ስለታዘዙ ብቻ ሲሰሩ በጣም አዝን ነበር። እናም አሁን እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ መናገር አልፈልግም። ደግሞም በእኔ መርህ መሠረት አንድ ሰው በፍርድ ቤት እስከሚፈረድበት ድረስ ንፁህ ሆኖ የመቆጠር መብት አለው። ስለዚህ አሁን እኔም ይሄነው ብዬ በትክክል የማውቀው ነገር የለም። የፍርድቤት እስኪያልፍ ድረስ በመንግሥትም፤ በእኛም በኩል ለፍርድቤቱ ነፃነትም ክብርና ንፅህና ሲባል በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠት ተገቢ አይመስለኝም።

አዲስ ዘመን፡- ኢዜማ ሲመሰረት ሕዝብ ከጣሰበት እምነት አንፃር እየሰራ አይደለም፤ እንዲያውም የመንግሥት ታማኝ ተቃዋሚ ሆኗል በሚል ይተቻል፤ እርሶ ይህንን አስተያየት እንዴት ያዩታል?

አቶ አንዷለም፡- እኛ አገር አየሽ ችግሩ ሁሉም ሰው የራሱ ጀግና ይፈልጋል። በራሱ አስተሳሰብና ምናባዊ እይታ ከአቅምሽ በላይ ይስልሻል። ከዚያም ጎልያድን አሳክሎ ይስልሽና መጨረሻ ላይ ያንን አላከለችም ብሎ መልሶ ይጥልሻል። ታዲያ ይህ የማን ችግር ነው? እኔ ሰው በሚስለኝ ልክ ልሆን አልችልም። እኔ መሆን የምችለው በአቅሜ ነው። ደካማውን እኔን ነው መሆን የምችለው። ሰዎችን ለማከል ብዬ ስወጣጠር አልኖርም። በአቅሜ፤ በችሎታዬ ያዋጣል በምለው መልኩ ነው የምሄደው። ፓርቲም ቢሆን የሚሉትን ለማከል ብሎ ሊወጣጠር አይችልም። ሰው ቁጭ ብሎ ተስፋ ሊያደርግና ሊሰንቅ ይችላል። በእኛ በኩል በአቀድነው መሠረት እየሄድን ነው፤ ስትራቴጂክ ግብ አስቀምጠናል። ዋነኛው ስትራቴጂክ ግባችን ደግሞ ለትውልድ የሚተርፍ ፓርቲ መፍጠር ነው። ፓርቲው ደግሞ የይስሙላ ሆኖ በሁለትና በሦስት ዓመት የሚጠፋ ሳይሆን ፈጣሪ ከረዳን ለረጅም ዘመን ለልጆቻችን መድህን የሚሆን የጠነከረ እየተሻሻለ የሚሄድ ፓርቲ ለማምጣት ነው እየሰራን ያለነው። ያንን ለመፍጠር ያደረግነው ጥረት ተሳክቶልናል ብዬ አምናለሁኝ። ብዙ ጥሩ ሥራ ሰርተናል። መድገም ከልሆነብኝ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ435 በላይ ወረዳዎች ላይ ተደራጅተናል። 278 ቢሮዎች ከፍተናል። ወደ 45 ፖሊሲዎችን እየሰራ ነው፤ 20ዎቹ ተጠናቋል። 19ኙ ደግሞ በጅምር ላይ ናቸው። ይህንን ሁኔታ ከአገራችን ሁኔታ አንፃር ስታዪው የትኛውም ፓርቲ ይህንን አያደርግም። ስለዚህ አሁን ግባችን ተሳክቷል።

ሁለተኛው ግባችን ደግሞ አገሪቱ ሰላም፣ መረጋጋትና ፍቅር እንዲሰፍን ማድረግ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ሲኖሩ ነው ዴሞክራሲ ሊኖር የሚችለው። ባልተረጋጋ አገር ላይ ዴሞክራሲም ሆነ ምርጫ ሊኖር አይችልም። ስለዚህ ጭቃ እየተቀባንም አገር እንዲረጋጋ እየሰራን ነው። አሁን ላይ ብልፅግናም ስትተቺ የብልፅግና ሰዎች መሳደብ ጀምረዋል። ብልፅግና ጥሩ ሲሰራ ያንንም እውቅና ስትሰጪ ሌላው ይሳደባል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የትኛውንም አቋም ይዘሽ የማትሰደቢበት ሁኔታ የለም። ስድብ እንደፖለቲካ ፋሽን ተወስዷል። እኔ በስድብ የተገነባ አገር አላውቅም። ችግር ካለ መወያየት ነው የሚያስፈገው። በእኛ አገር ያው ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው እንደሚባለው ሁሉ ኢዜማ ልክ የመንግሥት ተለጣፊ ተደርጎ እየተሳለ ነው። እኛ ግን የሚሉትን አይደለንም፤ እንዲያውም ነገ ከነገወዲያ ትልቁ ግብ ግብ ከእኛ ጋር እንዳይሆን ነው ስጋቴ።

በያዝነው መንገድ ግን አንናወጥም፤ እንፀናለን። አንዳንድ ጊዜ ማዕበሉ ወደእዚህ ሂጅ ሲልሽ የምትሄጂ ከሆነ፤ ከማዕበሉ ጋር አብረሽ የምትቀዝፊ ከሆነ አንቺ መሪ አይደለሽም። መሪ ማዕበሉን አቅጣጫ አስቀይሮ ወደ

ተከስቲ መስመር ናይ ሰላም ንምርግጋጽ ይሰርሕ ኣሎ።

ናይ ሰላም ኮሚሽን ኣብ ዝተፈላለዩ ከተማታት ዝተኻየደ ህዝባዊ ኣኼባ ኣብ ዝተገብረ ዘተ፡ ኣብ ከተማ ሰመራ ዝተፈጸመ ግጭት ብዙሓት ሰባት ህይወቶም ከምዝጠፍኣ ተገሊጹ።

ሸዬስ ዘመን «ዜና»

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት ውስጥ ከፍተኛ ባለስልጣናት ተሰብስበው ስለ ከተማዋ ጉዳይ ሲመክሩ ከርመዋል። ስብሰባው ከተጠራበት ዋና ምክንያት አንዱ ከተማዋ ውስጥ ያለውን የመሬት ወረራ ለመቆጣጠር ነው። ከተማዋ ውስጥ ያለው የመሬት ወረራ ከመጠኑ አልፎ ሰፊ ቦታ ላይ ደርሷል



...ዝኒ ዝኒ ዘሁ ሊሳ

ቀረጽ ናውለኝ መጽሐፍ ተሸላሚ የሆነችበት ሥራ ነው

ከተማ ገብረኪዳን፡- የመጀመሪያ ልቦለድ መጽሐፍሽ ተሸላሚ ሆነሻል፤ ስለ ሽልማቱ ምን ይሰማሻል?

ቀረጽ ናውለኝ፡- ሽልማቱ ከሚሰጠው ክብር በተጨማሪ ለቀጣይ ሥራዎቼ ትልቅ ተነሳሽነት ይፈጥርልኛል ብዬ አምናለሁ። ሽልማቱ ከሚሰጠው ክብር በተጨማሪ ለቀጣይ ሥራዎቼ ትልቅ ተነሳሽነት ይፈጥርልኛል ብዬ አምናለሁ።

ከተማ፡- ሽልማቱን ለመቀበል ስትሄጂ ምን ተሰማሽ?

ቀረጽ፡- ሽልማቱን ለመቀበል ስሄድ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል። ሽልማቱን ለመቀበል ስሄድ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶኛል

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመርቷል። ዶሴው የሚናገረው ታሪክ ግን ዛሬም ድረስ አለ። የተወሳሰቡ ወንጀሎች ከተራቀቁ የምርመራ ሂደቶች ጋር ዶሴው ውስጥ ናቸው። በዚህ ዓምድ ታሪካቸውን ልንሰማ የፈቀድናቸውን ዶሴዎች እንዲናገሩ ገልጠናቸዋል። የእውነተኛ ባስታሪኮችን ስም ማህበራዊ ሓላፊነት ወስደን ስደህንነታቸው ሲባል ቀይረናቸዋል።

የመቶአለቃው ድንበርተኞች

መልካምስራ አፈወርቅ

ሰሜን ወሎ ወልድያ የተወለደው ማናዬ ገዳሙ ልጅነቱ እንደ እኩዮቹ አልነበረም። ባልንጀሮቹ አመታትን በገፉበት የትምህርት ዓለም ርቆ አልተራመደም።ደብተር ይዞ ትምህርት ቤት መሄድ የቻለው እስከ አምስተኛ ክፍል ብቻ ነበር።

ማናዬ ዕድሜው ከፍ እንዳለ አርቆ ማሰብ ያዘ። በውስጡ የተመላለሰው ዕቅድ ወታደር መሆን ነበር። ያሰበው አልቀረም። ለሙያው የሚጠበቅበትን አሟልቶ የውትድርና ህይወትን ተቀላቀለ። ብቁ ወታደር ለመሆን ወራትን የቆጠረበት የስልጠና ጊዜ ቀላል የሚባል አልነበረም።ከልጅነት አቅሙ ጋር ተዳምሮ ፈታኝ ሆነበት።

ማናዬ የቆመበት ዓላማና ግብ ጠንካራ ሆኖ ወታደራዊ ስልጠናውን በስኬት አጠናቀቀ።ከምርቃቱ በኋላ ወደጃንሜዳ ማምራት ነበረበት። በርካቶች በወታደራዊ ልብሳቸው ደምቀው በሚታዩበት በዚህ ስፍራ ብዙ ግዳጆች ይከወናሉ። ማንኛውም እንቅስቃሴ በወታደራዊ ስነ-ስርዓትና በተቀመጡ ህግና ደንቦች ይዳኛል።መማር፣ መሰልጠንና ማወቅ የሚሻ አባልም ተጠቃሚ ለመሆን ቅርብ ነው።

ለማናዬ የጃንሜዳ ቆይታው ከውትድርና የዘለለ ተጨማሪ ዕድል አስገኝለት።የጤና ረዳትነት ትምህርት ተከታትሎ የነርስነት ሙያን ያዘ።ከዚህ በኋላ የወጣቱ ጉልበት በረታ። በየክልሉ እየዞረ በተማረበት ሙያ ወገኖቹን ማገልገል ቀጠለ።

ግዳጅ በጦርሜዳ...

በ1992 ዓ.ም የኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ጦርነቱን ተከትሎም በርካቶች በሙሉ ፍላጎትና ወኔ ወደጦርሜዳ ተመሙ።ጦርነቱ መራርና የህይወት ዋጋን የሚያስከፍል ነበር።ይህ አጋጣሚም ማናዬን የመሰሉ የህክምና ባለሙያዎችን እገዛ የሚጠይቅ ሆነ።ወጣቱ ነርስ መህል ጦር ሜዳ ውሎ ግዳጁን መወጣት ቻለ።በስልጠና የተካነ ወታደርና በሙያው የበቃ ነርስ መሆኑ ስኬታማ አደረገው ::

ከጦርሜዳ መልስ ...

በ1995 ዓ.ም፣ ማናዬ ተመልሶ አዲስ አበባ ገባ።በዚህ ወቅት በሁለቱ ሀገሮች መካከል ሲካሄድ የቆየው ደም አፋሳሽ ጦርነት ተጠናቆ ነበር።መቶ አለቃ ማናዬ ግዳጁን ፈጽሞ እንደተመለሰ ጊዜ ወስዶ ከራሱ መከረ።ከዚህ በኋላ በነበረበት ስራ መቀጠል እንደሌለበት ሲያስብበት ከርሟል።ይህ ይሆን ዘንድም ከሰራዊቱ በክብር መሰናበት ፈልጓል::

ውሎ አድሮ የማናዬ ሀሳብ ተቀባይነት አገኘ። ጥያቄውን በአግባቡ ያጤነው ክፍል እንደደንቡ «ይገባዋል» ያለውን አሟልቶ በክብር እንዲሰናበት ፈቀደ። መቶ አለቃው ዕድሜውን በደምና ላብ አዋዝቶ ዋጋ የከፈለበትን የወታደር ቤት ለቀቀ። ነገን ባሻገር እያየም ለሌላ ሕይወት ተዘጋጀ::

ማናዬ ወታደር ቤት እያለ ያገኛቸውን የጦር መሳሪያዎች ከአጠገቡ ማራቅ አልፈለገም።ለራስ መጠበቂያ ሲል በእጁ ያስገባው ክላሽ፤ ማካሮቭና ኮልት ሽጉጥ፤ የጦር ሜዳ መነጽር፣ የውትድርና ልብሶችና ሌሎችም መሳሪያዎች አብረውት ናቸው::

አዲስ መንገድ...

አሁን ማናዬና ውትድርና በወጉ ተለያይተዋል። ከስራው በተሰናበተ ማግስትም ከአንድ የግል ድርጅት በሾፌርነት ተቀጥሮ ወፍራም ደመወዝ ማግኘት ጀምሯል። ቀድሞ በስራው ልምድ ያነበረው ሰው ከብዙዎች ተግባብቶ ሙያውን እንጀራ ለማድረግ አልዘገየም::

ሾፌርነት መተዳደሪያው ከሆነ ወዲህ በስራው በርትቶ የራሱን መኪና ገዛ። በቂ ገንዘብም ከባንክ አኖረ። ይህን ሲያደርግ «የኔ» የሚለው መኖሪያ አልነበረውም። ውሎ አድሮ ግን የፍላጎቱ የሚሞላበት ቀን ደረሰ። ችግሩን ጠቅሶ ጥያቄ ያቀረበበት ቀበሌ «ይገባሀል» ያለውን ቤት «እነሆ» ሲል አስረከበው::

ማናዬ በርከት ያሉ ነዋሪዎች ከሚገኙበት ግቢ ደርሶ ቤቱን ተመለከተ። ይዞታው ለእሱ ኑሮ የሚያንስ አይደለም። ዙሪያ ገባውን ግን የወደደው አይመስልም። ብዙዎች በጉርብትና የሚኖሩበት ጊቢ የጋራ መሆኑ ለአዲሱ እንግዳ አልተመቸውም::



ከአመታት በኋላ...

ማናዬ በተረከበው የቀበሌ ቤት መኖር ከጀመረ አመታት ተቆጥረዋል። ግቢው በርካቶችን የያዘ ፣ማህበራዊነት የበዛው፣ ድምጽና ጫጫታ የማያጣው ነው።ከእሱ በስተግርጌ አንድ ቤት በአጭር ርቀት ያዋስነዋል። ቤቱ እንደሌሎቹ የቀበሌ አይደለም።በግል ይዞታ የተመዘገበና በርከት ያሉ ቤተሰቦችን የሚያኖር ነው::

ማናዬና ይህ ቤተሰብ በቦታ ይገባኛል ጥያቄ ሲወዛገቡ አመታት ተቆጥረዋል። የሁለቱን ወገኖች አለመግባባት ተከትሎ በተነሳ ተመሳሳይ ፍላጎትም ማናዬ ከሌሎች ጎረቤቶቹ ጋር ሰላም ኖሮት አያውቅም ። በጠብና ጭቅጭቅ ውሎ የሚያድርው ግቢ መቀያየምን አዝሎ በእርቅና ሽምግልና ሲዳኝ ይውላል::

የማናዬን ግድግዳ የሚጋሩት ባልና ሚስት በይዞታቸው ስር ያለውን ከፍት ጓሮ ሲጠቀሙበት ኖረዋል። ማናዬ የቀበሌ ቤቱን ተረክቦ መኖር እንደጀመረ ቦታውን በ«ይገባኛል» ጠይቆ ውዝግብ ተፈጥሯል። በየቀኑ የሚነሳው ግጭት ዛቻና ማስፈራሪያ ታክሎበት የጎሪጥ እያተያየ ነው::

አለመግባባቱ ስር ሰዶ ጠቡ መካረር እንደያዘ ሁለቱም ወገኖች ለቀበሌው አቤቱታ ማስማት ጀመሩ። ማናዬ ቤት ማደሱን ተከትሎ ቦታውን ማጠሩ ያበሳጫቸው ባልና ሚስት ስፍራው የግላቸው መሆኑን አስመስከሩ። «ጉዳያቸው አግባብ አይደለም» ያለው ማናዬም ያስቀመጡትን ዕቃ እንዲያነሱለት ደጋግሞ ጠየቀ። በይገባኛል ውሳኔው ጸንቶም «አሻፈረኝ » ሲል ሞገተ ::

የግቢው ዕለታዊ ጭቅጭቅና ጠብ ቀጥሏል።በቅርብ ርቀት የሚተያዩት ጠበኞች መህል ሰላም ውሎ ማደር ብርቅ ከሆነ ቆይቷል። በየቀኑ የሚካሰሱት ድንበርተኞች ሲወሰንባቸውና ሲወሰንላቸው፣ ሲጣሉና ሲታረቁ ፣ አመታትን ያለ መፍትሄ ዘልቀዋል።

አንዳንዴ በሽማግሌዎች እርቅ በሆነ ጊዜ ግቢው ሰላም ሆኖ ይሰነብታል። ይህ ክራሞት ግን እምብዛም አይዘልቅም። የአንዳቸው ፍላጎት በአንዳቸው ሲበለጥ የጠቡ እሳት ተጭሮ ነገር በግቢው ይነዳል። ጉዳዩም ከባለጉዳዮቹ አልፎ ሌሎችንም ያነካካል።

አንድ ቀን ማናዬ በድንገት ተነስቶ ቤቱን ማደስ ጀመረ። እድሳቱ የቤቱን ይዞት የሚቀይርና የሌሎችን ይዞታ የሚጋፋ ነበር። ይህን ያወቁ የግቢው ነዋሪዎች ድርጊቱን እንዲያቆም ጠየቁ። የሰማቸው የለም። ኩሽናና መጸዳጃን መጠቀም ያልቻሉ ጎረቤቶቹ፣ ማናዬ ለራሱ ማለፊያ የከለለውን አጥር በመቃወም ጮሁ። ክፉ ደግ ተናገሩ። ጩኸታቸው መፍትሄ አልባ ሆነ::

አሁን የማናዬና የባልና ሚስቱ ክስ በቀበሌና በፖሊስ ጣቢያ ቀጥሏል። ጉዳዩ በነዚህ አካላት የ«ተስማሙ» ሀሳብ ብቻ የሚፈታ አልሆነም። ስር የሰደደው ጭቅጭቅ ድንበርተኞቹን ዶሴ አስከፍቶ ፍርድቤት ደጃፍ ያመላልሳቸው ይዟል::

ከሳሽና ተከሳሽ ሆነው የቀረቡት ጎረቤታሞች በ«ይገባኛል» ውዝግብ የራሳቸውን መከራከሪያ ይዘው ሙግታቸውን ቀጠሉ። የተባለው ቦታ ፍትህ ይሰጥበት ዘንድም በየግላቸው «አቤት» ሲሉ ፍርድቤቱን ወተወቱ።

ጊዜያትን ያስቆጠረው የድንበርተኞቹ ውዝግብ በየቀኑ በጠብ መታጀቡ አልቀረም።ማናዬ ሲወጣና ሲገባ የሚያገኘውን የቤቱን አባወራ እየጠበቀ ከመዛት ባለፈ በሽጉጥ ማስፈራራቱን ቀጥሏል። በዚህ ብቻ አልቆመም። ሌሎች ጎረቤቶቹ ጭምር የሽጉጥ አፈሙዝ ተደግኖባቸው «እገላችኋለሁ» በሚል ማስፈራሪያ ስጋት ውስጥ ገቡ ።

የማናዬ ድርጊት ከፍርሀት ጥሎ ዕንቅልፍ የነሳቸው የግቢው ነዋሪዎች በጋራ መምከር ጀምረዋል። ይህ ሰው በዚህ ከቀጠለ ለህይወታቸው እንደሚያስጋ አልጠፋቸውም።ይህንኑ በሚያስረዳ የደብዳቤ አባሪም ፊርማ አሰባስበው ለሚመለከተው አሳውቀዋል።ወሬውን የሰማው ማናዬ በጎረቤቶቹ ቂም ይዟል ።ባያቸው ጊዜም ጥርስ እየነከሰ ማስፈራራቱን ቀጥሏል::

ማናዬ የቤት እድሳቱን እንዳበቃ መተላለፊያውን ለማስከበር አጥሩን ማሳጠር ጀመረ።የጓሮውን መታጠር ያዩ ባልና ሚስትም ጎረቤታቸው ከድርጊቱ እንዲታቀብ አሳሰቡ።መግባባት አልቻሉም።ማናዬ የጀመረውን እንደሚቀጥል ገልጾ ስራውን አጠናቆ አሳያቸው::

ድርጊቱ መብታችንን ተጋፍቷል፤ ያሉት ጥንዶች የጀመሩትን ክስ ለመቀጠል ወደ ፍርድ ቤት አመሩ። አቤቱታቸውን አቅርበው ማስረጃ አሳይተው ምስክሮች ጠሩ።ፍርድቤቱ የሁለቱን ጉዳይ ግራ ቀኝ መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ጊዜ ቀጠሮ ሰጠ::

የካቲት 24 ቀን 2006 ዓም..

ቀኑ ቀትርና ጸሐያማ ነው። የፍርድ ቤቱ ውሎ በቀጠሮ እንደተቋጨ ባልናሚስት ወደ ቤታቸው አቅንተዋል።በርካቶች የሚኖሩበት ግቢ ዛሬም ከወትሮ የተለየ አልሆነም። ህጻናት፣ ከወዲያ ወዲህ እየሮጡ ይጫወታሉ። ነዋሪዎች በተለመደ እንቅስቃሴ ውስጥ ናቸው። ጥንዶቹ ቤታቸው እንደገቡ በጎረቤታቸው የተከለለውን ጓሮ አሻግረው ተመለከቱ። በስፍራው የቆመ አንድ አናጺ አጥሩን እያጠባበቀ ነው። ሁለቱም በንዴት በገኑ። የግል ይዞታቸው በማይገባው የቀበሌ ነዋሪ መደፈሩ አበሸቃቸው::

ከደቂቃዎች በኋላ ባልና ሚስት በጎረቤታቸው የታጠረውን አጥር ማስፈረስ ጀመሩ። ይህን የሰማው ማናዬ ከወጣበት በፍጥነት ተመልሶ መጣ።እየሆነ ያለውን ተመልክቶም ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ጠየቀ። አልተግባቡም:: ጭቅጭቅ ተጀመረ።

ማናዬ በጥንዶቹ ድርጊት እየበሸቀ ከግቢው ተጣድፎ ወጣ። ከአፍታ በኋላም ሁለት ፖሊሶች አስከትሎ ተመለሰ። ፖሊሶቹ ድርጊቱን ለማርጉብ የአጥሩ ፈረሳ እንዲቆም ጠየቁ።ጉዳዩን በወጉ መፍታት አልቻሉም።ግቢውን ለቀው ከአካባቢው ራቁ።መፍትሄ ያጣው ማናዬ ጸጉሩን እየነጨ፣ጥርሱን እያፋጨ ወደቤቱ ገብቶ በሩን ደረገመ::

በንዴት የጋለው ሰው የተለየ ሽንፈት ተሰምቶታል። ጉዳዩን ባልፈቱት ፖሊሶችና በጎረቤቶቹ ድርጊት ውስጡ እየበገነ ነው:: ይህን ስሜት እያስታመመ መቆየት አልፈለገም። ሽሽነ ያኖረው ክላሽንኮፕ መሳሪያ ትዝ አለው። ጥይት አቅሞ በትከሻው አንግቦ ለመውጣት ጊዜ አልፈጀም ።

ዓይኖቹ እየቃበዙ ግራቀኙን አሰሰ። የቅርብ ጎረቤቱን አላጣውም። እያሯሯጠ፤ አነጣጥሮ ተኮሰ ። ጥይቶቹ አንድ... ሁለት.. ሶስት... አራት... እያሉ ተቆጠሩ። ተኳሹ ታላሚውን ከጥሻ ስር ጣለው። ዒላማቸውን ያልሳቱ ጥይቶች በአካሉ አርፈው እንዳይሆን አደረጉት::

ማናዬ በዚህ የበቃው አይመስልም።አሁንም ማለም መተኮሱን ቀጠለ። አምስት.. ሰድስት..ሰባት..ስምንት... ሀያ ጥይቶች በባላንጣው አካል ላይ ተከታትለው አረፉ። መሳሪያው የጎረሰውን ተፍቶ ሲጨርስ ግቢው በጸጥታ ተዋጠ::

ሚስት በድንጋጤ ትይዘው ትጨብጠው ጠፋት። የባለቤቷን አሰቃቂ ሞት በአይኗ ያሳያት ሰው እሷን እንደማይለቃት አወቀች።ብርክ እንደያዛት ላብ እያጠመቃት ወደቤቷ ሮጠች። ቦታ መርጦ፣ ስፍራ ለይቶ ለመደበቅ ቦታ ጠበባት::

ወይዘሮዋ አልጋስሩን፤ የበሩን ጀርባ፣ የጓዳውን ጥግ በእይታ አሰሰችው። ከውጭ የተጣደፈ ኮቴ ወደ እሷ ሲቀርብ ይሰማታል። እንደምንም ተንፏቃ ከወንበሩ ስር ገባች። በርከት ያሉ ልብሶች ከእጇ ደረሱ።በልብሶቹ ተሸፋፍና፣መላ አካሏን ጠቅልላ ትንፋሽዋን ሰበሰበች። የሰማቸው ኮቴ ሳሎኑን አልፎ አጠገቧ ሲደርስ ታወቃት::

ማናዬ ሀያ ጥይቶችን እንደተኮሰ መሳሪያው የቃመውን እንደጨረሰ ተረዳ። ጊዜ አላጠፋም:: እየተጣደፈ ወደቤት ተመለሰና ሌላ ካርታ አውጥቶ ተጨማሪ ጥይቶች ጨመረ። በሩን በርግዶ ሲገባ እማወራዋ ከእጁ እንደማታመልጥ ገምቷል::

በዓይኖቹ ጥቂት ማትሮ ልብስ የተከመረበትን የወንበር ስር ገለጠው። ተፈላጊዋ እየተንቀጠቀጠች ሽጉጥ ብላ አገኛት። ክላሹን ወድሮ ቃተውን ፈጥኖ ሳበው።ጥይቶቹ አንድ..ሁለት..ሶስት...እያሉ አስራአንድ ጊዜ ጮሁ። ግዳዩን የጨረሰው ተኳሽ ከደጅ ወጥቶ ጎረቤቶቹን ፈለገ። አንዳቸውም በስፍራው የሉም። በንዴት ጥርሱን ነከሰ። ደም የለበሱ ዓይኖቹ ቃበዙ።

የፖሊስ ምርመራ ...

ፖሊስ መካኒሳ «ጉልት» ከተባለ ሰፈር፡ ደርሶ ግቢውን ሲቆጣጠር አካባቢው በተለየ ጸጥታ ተውጦ ነበር። ማናዬ በፖሊስ መከበቡን እንዳወቀ ለማምለጥ አልሞከረም። እጁን ለህግ ሰጠ። ወዲያው በፍርሀት የራዱ የግቢው ህጻናትና ነዋሪዎች ከተደበቁበት ወጡ።ፖሊስ የሚቾቹን አስከሬን እንዳነሳ ምርመራውን ቀጠለ። ባልና ሚስቱ የሶስት ህጻናትና የአንዲት ወጣት ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ወላጆች ነበሩ::

ጉዳዩን የያዘው መርማሪ ሳጅን ግሩም ታረቀኝ የግለሰቡን የዕምነት ክህደት ቃል ተቀብሎ ለዓቃቢህግ ክስ መዝገቡን አሳለፈ:: ተጠርጣሪው ክስ ተመስርቶበት ፍርድ እስኪሰጠውም በቂሊንጦ ማረሚያ ቤት እንዲቆይ ተደረገ። እንዲህ በሆነ ጥቂት ጊዚያት ግን አንድ አስደንጋጭ ወሬ ተሰማ። መቶ አለቃ ማናዬ ከማረሚያቤት ማምለጡ ታወቀ። የግቢው ነዋሪ ዕንቅልፍ አጥቶ ከረመ። ፖሊስ በፍለጋ አሰሳውን ቀጠለ። ከቀናት በአንዱ ቀን ማናዬ በአዲስ አበባ ስቴድየም ኳስ ለማየት በተቀመጠበት በቁጥጥር ስር ዋለ::

ውሳኔ..

ህዳር 9 ቀን 2008 ዓ.ም ችሎቱ የተሰየመው የልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆን ብሎ ሰው በመግደል ወንጀል የተከሰሰውን ግለሰብ የመጨረሻ ፍርድ ውሳኔ ሊሰጥ በቀጠሮው ተገኝቷል። ፍርድቤቱ በቀረቡለት ማስረጃዎች ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ በሰጠው ውሳኔም መቶ አለቃ ማናዬ ገዳሙ በዕድሜ ልክ እስራት እንዲቀጣ ሲል ውሳኔ አስተላልፏል።

Հայկական ժամանակ



ԱՐՁԱԿՈՒՆ

ԳԻՇԵՐՈՒՄ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ԵԿԵՂԵՑՈՒ ՏՈՆԱԿԱՏՈՒԹՅԱՆ ԱՌԹԻՒ ՀԱՆԴԻՊՈՒՄՆԵՐ

Գիշերուան ժամերուն Հայկական Կաթողիկէ Եկեղեցւոյ տոնակատարութեան առթիւ Ս. Աստուածածին մայր տաճարին մէջ հանդիսաւոր պատարագ մատուցուեցաւ, որուն ներկայ գտնուեցան Հայրապետական փոխանորդ Գերաշնորհ Տ. Նարեկ արքեպիսկոպոս Ալճեան, Գերաշնորհ Տ. Գրիգոր արքեպիսկոպոս Պետրոսեան, Գերաշնորհ Տ. Գրիգոր արքեպիսկոպոս Պալեան, Գերաշնորհ Տ. Գրիգոր եպիսկոպոս Ահարոնեան, Գերաշնորհ Տ. Գրիգոր եպիսկոպոս Պետրոս

የመገናኛ ብዙሃን የክፍያ ጣቢያዎችን ያስተዋወቁ እንስት

ጌትነት ተስፋማርያም

ለኢትዮጵያውያን አዲስ የነበረውን የክፍያ ቴሌቪዥን ጣቢያ አሰራር በሀገር ውስጥ በማስተዋወቅ ረገድ ስማቸው ጎልቶ ይነሳል። ድርጅታቸውን በብቃት ለመምራት በመቻላቸው ሴት ልጅ ሰርታ ማሳራት ትችላለች የሚለውን በተግባር አሳይተዋል። ተግባቢ እና ለመቀራረብ ቀለል ያሉ ሰው መሆናቸውን ደግሞ የሚያውቋቸው ይመሰክሩላቸዋል። የዛሬዋ ባለታሪካችን ወይዘሮ ገሊላ ገብረሚካኤል።

ወይዘሮ ገሊላ የተወለዱት በአዲስ አበባ ነው። ለቤተሰባቸው የመጀመሪያ ልጅ ሲሆኑ አራት ወንድምና እህቶችም አሏቸው። በአዲስ አበባ አሮጌው ኤርፖርት ያደጉት እኚህ እንስት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት ሴቶች ብቻ በሚማሩበት ናዝሬት ስኩል ትምህርት ቤት ነው።

ከልጅነታቸው ጀምሮ አባታቸው መጽሐፍትን እንዲያነቡ እና የገሃዱን ዓለም በውብ ታሪኮቻቸው የሚያሳዩ ድርሰቶችን እንዲያነቡ ማድረጋቸው በአፍላ እድሜያቸው ስለ ህይወት ምንነት እንዲገነዘቡ እንዳገዛቸው ይናገራሉ። አምስተኛ ክፍል እያሉ ፍቅር እስከ መቃብር፣ አንድ ለእናቱ የተሰኙ የአማርኛ ድርሰቶችን እና ከውጭ ሀገራት ደግሞ የነሼክስፒርን ተውኔቶች ጭምር ማንበባቸውን ያስታውሳሉ።

አባታቸው መጽሐፍቱን ሲያቀርቡላቸውም በዚህች ዓለም ላይ ውጤታማ ለመሆን ከብርቶዎች መካከል ቁንጮ ሆነው መውጣት እንዳለባቸውም እያስተማሩ በመሆኑ ሲያድጉ ለተሻለ ለውጥ እንዲነሳሱ ያገዛቸውን ስንቅ እንዳስያዟቸው አይዘነጉትም። እናታቸውም በበኩላቸው ደስታ የሚገኘው ከእራስ ማንነት መሆኑን አስረግጠው በማስረዳት በሴትነታቸውም ከጥገኝነት ወጥተው መምራት የእራሳቸውን ንግድ እንደሚችሉ እምነት አሳድረውባቸዋል።

ከንባብ ባህል ጋር ተቆራኝተው ያደጉት ወይዘሮ ገሊላ በትምህርታቸው ደግሞ ለማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች ያደሉ እንደነበር አይዘነጉትም። በደርግ ዘመነ መንግስት የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ለከፍተኛ ትምህርት ከበቁ ጥቂት ሴት ተማሪዎች መካከል ሆነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ተቀላቀሉ።

በዩኒቨርሲቲው ቆይታቸው የህግ ትምህርትን ምርጫቸው አድርገው አጥንተዋል። በክረምት ወቅት ደግሞ የተለያዩ የልምምድ ስራዎችን እንዲሰሩ አባታቸው ስለሚያበረታቷቸው የእረፍት ጊዜያቸውን በስራ ነበር ያሳለፉት።

የከፍተኛ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከተመረቁ በኋላ ደግሞ ወዲያውኑ ጎፋ አካባቢ በሚገኘው ያኮና ኢንጂነሪንግ በተሰኘው ተቋም ውስጥ በ400 ብር የወር ደመወዝ ተቀጠሩ። በወቅቱ የስራ አስኪያጁን የኮንትራት ውሎች፣ የስራ ቅጥሮችን እና የደንበኛ አገልግሎት ሰነዶችን በማዘጋጀት እንዲሁም ተያያዥ ስራዎችን በመከወን ጥሩ ተቀባይነት አትርፈው ነበር።

ከዚህ ስራቸው በተጓዳኝነት ደግሞ ተማሪዎችን በማስጠናት እና ጥሩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ቸሎታቸውን በመጠቀም የአስተረጓሚነት ስራ ይከውኑ እንደነበር ያስታውሳሉ። በተለይም ከውጭ የመጡ ሰዎችን ይዘው መላ ኢትዮጵያን ለአንድ ወር በመዞር የአስተረጓሚነት ስራ ያከናነወኑበት ጊዜ ትልቅ ልምድ ያገኙበት እንደሆነ አይዘነጉትም።

የያኮና ኢንጂነሪንግ ስራቸውን ከስድስት ወራት ቆይታ በኋላ ሲጠናቀቅ ደግሞ ኢትዮ ሳተላይት የተባለ ተቋም ውስጥ ተቀጥረው መስራት ጀመሩ። በደርግ ዘመነ መንግስት የሳተላይት ዲሽ ቴሌቪዥ ጣቢያ የሚፈቀደው ለኤምባሲዎች እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ብቻ በመሆኑ ግንኙነታቸው በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሀገራት ሰዎች ጋር ሆነ።

በሆቴል ደረጃ ደግሞ ሳተላይት መቀበያ የነበረው ጊዮን ሆቴል ላይ በመሆኑ የቴክኖሎጂ ገጠማ እና ዲሽ ጥገናው የሚከናወነው ከቴሌኮም ኩባንያው ፈቃድ ሲገኝ እንደነበረ ያስታውሳሉ። ወይዘሮ ገሊላም ሴልስ ማናጀር ሆነው በተቋሙ ቢቀጠሩም ኤምባሲዎች እና የተለያዩ ዲፕሎማቲክ መቀመጫዎች ድረስ በማምራት እና አስፈላጊ ሲሆን ከቴክኒሻኖች ጋር የቤቶች ጣሪያ ላይ ጭምር በመውጣት የሳተላይት ቴሌቪዥን መሳሪያዎች ገጠማ እና ጥገና ላይ መሳተፍ ጀመሩ።

ከዚህ ባለፈ የኢትዮ ቴሌኮም ኩባንያ ድረስ በመመላለስ እያንዳንዱ የቴክኖሎጂ ገጠማ ስራ ፈቃድ በማውጣት እና ውሎችን በማዘጋጀት ስራቸውን በብቃት መምራት ችለው ነበር። ለሙያው ፍቅር ስለነበራቸው በትርፍ ሰዓታቸውም ጭምር በስራ ላይ በማሳለፍ ከድርጅቱ ባለቤት ባገርሽ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ጠንካራ አደረጉ።

በጠንካራ ሰራተኝነታቸው እና የቢዝነስ ሃሳባቸው ከድርጅቱ ባለቤት ጋር የተሻለ ስራ መስራት እንደሚችሉ በማመን በሽርክና አንድ የጋራ ካምፓኒ ለመክፈት ወሰኑ። የድርጅቱን ስም ሀብሩ ብለው በመሰየም የደቡብ አፍሪካው ጣቢያ የመልቲቾይስ ዲኤስ ቲቪ የኢትዮጵያ ኤጀንት ሆነው መስራት ጀመሩ። ወይዘሮ ገሊላም ከተቀጣሪነት ወደ ስራ ፈጣሪነት በመቀየር በጋራ ከሸሪካቸው ጋር የመሰረቱትን ድርጅት መምራት ጀመሩ።



የንግድ ፈቃድ ሲያወጡ የቴሌቪዥን ስርጭትን ተቀበሎ በከፍያ ለማስተላለፍ ፍቃድ የሚሰጥ አካል ባለመኖሩ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን እስኪቋቋም ድረስ በኮሚሽን ኤጀንት ስር ተመዝግበው በኢትዮ ቴሌኮም ቁጥጥር ስር ሆነው ስራቸውን ጀመሩ።

የንግድ አጋራቸው ደግሞ በሌላ የንግድ ስራ ስለሚጠመዱ ወይዘሮ ገሊላ ተቆጣጣሪ እራሳቸው የሸያጭ ባለሙያ እና ጉዳይ አስፈጻሚም ሆነው አብዛኛውን ስራ ይመሩ እንደነበር ያስታውሳሉ።

በአጋራቸው የቡና ማበጠሪያ ድርጅት ግቢ ውስጥ የሚገኝ አንድ አንድ አነስተኛ ክፍል ተሰጥቷቸው የመልቲቾይዝ ዲኤስ ቲቪ የክፍያ ቴሌቪዥን ስርጭቶች በየቤቱ እንዲገቡ ከአውሮፓውያኑ 2016 ጀምሮ ጥረት ማድረጋቸውን ያስታውሳሉ።

በወቅቱ በቂ ደመወዝ እንኳን የሌላቸው ቢሆንም ወደፊት ትልቅ ስኬት የሚታይበት ዘርፍ መሆኑን በማመን ተስፋ ሳየቆርጡ ለመስራት ወሰኑ። የንግድ አጋራቸውም ገፍተው እንዲቀጥሉበት እና ስራው በቀጣይ ዓመታት ትልቅ ገቢ የሚገኝበት እንደሚሆን በማበረታታት አጋርነታቸውን አሳዮአቸው።

ወይዘሮ ገሊላም በየአካባቢውም እየዞሩ ስለክፍያ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በማስረዳት እና የሳተላይት መቀበያ ዲኮደሮችን በማቅረብ ንግዳቸው መሰረት እንዲይዝ እንቅስቃሴያቸውን ገፉበት። በወቅቱ የጣሊያን እና ሌሎች የዓለም አቀፍ ኮሚዩኒቲ ማህበረሰቦች እና የአፍሪካ ህብረት የዲኤስቲቪ ስርጭቶችን ከፍለው ለመጠቀም የዲሽ መቀበያዎችን መረከብ በመቻላቸው ጥቂት ገቢ መገኘት ጀመረ።

ስራውን ማስተዋወቅ ሲጀምሩ እና ሳተላይት ተቀበሎ ቴሌቪዥን ማሰራጨት በሀገር ደህንነትም ሆነ በቴሌኮም ስራ ላይ የሚያመጣው ጉዳት እንደሌለ ግንዛቤ መፈጠር ሲጀምር ከኤምባሲዎች እና የውጭ ሀገራት ሰዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን ግለሰቦችም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ተፈቀደ።

በዚህ ወቅት የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ቁጥር ወደ 120 በማደጉ የነወይዘሮ ገሊላ ንግድ ገቢውም በጥሩ ሁኔታ አደገ። ቦሌ ፒኮክ አካባቢ የሚገኝ ቢሮ ተከራይተው ከራሳቸው በተጨማሪ አራት ሰራተኞችን ቀጥረው ንግዳቸውን አጠናከሩ። በወቅቱ የሳተላይት መቀበያውን ገጠማ የሚያከናውኑ ሁለት ሰራተኞቸ በማሰልጠን ጭምር አብረዋቸው እንዲሰሩ አድርገዋል።

የዲኤስቲቪን ስርጭቶች በክፍያ በመግዛት ከውጭ ሀገራት የሚተላለፉ ትምህርታዊ፣ መዝናኛ እና የስፖርት ዝግጅቶችን መከታተል የሚፈልጉ ዜጎችም ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እያደገ መጣ። እ.አ.አ በ2000 ላይ ደግሞ የእነወይዘሮ ገሊላን ንግድ በእጅጉ የሚያሳድግ አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ።

የደቡብ አፍሪካው የሳተላይት ጣቢያ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ የእግር ኳስ ውድድሮችን በኢትዮጵያ በቀጥታ ማስተላለፍ የሚችልበትን ፈቃድ አገኘ። ወይዘሮ ገሊላም ይህን እድል በመጠቀም የስፖርት አፍቃሪውን ህዝብ ፍላጎት ለማርካት ድርጅታቸው የሳተላይት መቀበያ ቴክኖሎጂ እቃዎችን ከማቅረብ ባለፈ በገጠማ ስራውም እንደሚሳተፍ በሰፊው አስተዋውቋ። የከፍያ ጣቢያውን የሚጠይቀውን የወር ክፍያ መሰብሰባቸውን ቀጠሉ።

በርካታ መዝናኛ ስፍራዎችም የዲኤስቲቪን አገልግሎት በእነወይዘሮ ገሊላ ድርጅት አማካኝነት በማግኘት የእግርኳስ ውድድሮችን በቀጥታ እያሳዩ ገቢ ወደማግኘት ተሸጋገሩ። ኳስ ብቻ ማሳየት የሚፈልጉ አነስተኛ የንግድ ቤቶችም በየቦታው እንደአሸን በመፍላታቸው የሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጭት አገልግሎቱ እና ቴክኒክ ስራው በፍጥነት አደገ።

በወቅቱ ወይዘሮ ገሊላ ከመርካቶ አከፋፋዮች ጋር በመጣመር የሳተላይት መቀበያ እቃዎችን በማቅረብ መገዱን ተያያዙት። መቀበያ እቃዎቹን የሚገዙ ሰዎች ከደቡብ አፍሪካ ለሚተላለፈው የቴሌቪዥን ስርጭት በየወሩ በሚታሰብ ከፍያ በብር እይከፈሉ ለመልቲቾይዝ ኢትዮጵያ ያስረከባሉ። የወይዘሮ ገሊላ መልቲቾይስ የኢትዮጵያ ክፍል ከዋናው ማሰራጫ ተቋም ጋር በማኖረው ስምምነት በየዓመቱ ስርጭቱን በማስተላለፍ ጠቀም ያለ ገቢ ማግኘቱን ቀጠለ።

በዚህ ወቅት በመላ ኢትዮጵያ አገልግሎቱን የሚያገኙ ደንበኞች ቁጥር በሺዎች ማደግ ጀመረ። ከአገልግሎቱ ጋር ተያይዞ ደግሞ በየአካባቢው የዲኤስቲቪ አገልግሎት የዲሽ ገጠማ እና ቴክኒክ ስራ የሚከውኑ ወጣቶችም የስራ እድል ተፈጠረላቸው። ወጣቶቹን በየጊዜው በማሰልጠን እና ልዩ ክህሎት የሚጠይቀውን የዲኤስቲቪ ዲሽ ጥገና ስራ በማለማመድ ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ እድሉን አመቻቹ።

አዲስ አበባ ላይ ማዕከሉን ያደረገው ድርጅት አሁን ላይ በአምስት ጥቅል/ፓኪጆች/ የተከፋፈለ የክፍያ ስርዓት ያለው የሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጭትን ከደቡብ አፍሪካ ተቀብሎ በኢትዮጵያ እያቀረበ ይገኛል። እንደየጥቅል አገልግሎት እና ደንበኞች ምርጫም በየወሩ ከ220 ብር ከፍያ አንስቶ ከሁለት ሺ ብር በላይ የሚጠይቁ የክፍያ ጣቢያ አማራጮችንም አቅርቧል።

በተለይ ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተዘጋጁ ጎጆ ቤተሰብ እና ሜዳ የተሰኙ የጥቅል አማራጮችን በክፍያ እያስተላለፉ ይገኛሉ። በመላ ሀገሪቷ የሚሰራጩ የሳተላይት መቀበያ እቃዎችን ለማቅረብም 10 ዋና ኤጋሮችን እና ከ270 በላይ አነስተኛ የኤሌክትሮኒክስ እቃ አቅራቢዎች ጋር በፈጠሩት የንግድ ጥምረት ምርታቸው ያቀርባሉ።

በእድገት ላይ እድገትን እየጨመረ የመጣው ድርጅታቸው አሁን ላይ ከውጭ ሀገራት ከሚተላለፉ ጣቢያዎች በተጨማሪ በጋራ ጥቅም ላይ በተመሰረተ የክፍያ ስርዓት 13 የኢትዮጵያውያን ቴሌቪዥን ጣቢያዎችን በስርጭት ጥቅሎቻቸው በማካተት በመልቲቾይስ ዲኤስቲቪ ስርጭቶች በሉል እያስተላለፉ ይገኛል።

የአማርኛ ሙዚቃዎችን በአፍሪካውያን ዘንድ ለማስተዋወቅም ትሬስ ሙዚቃ የተሰኘ የኢትዮጵያውያን ስራዎች ብቻ የሚተላለፉበት ጣቢያም በአየር ላይ እንዲውል አድርገዋል። በቀጣይ ደግሞ የኢትዮጵያውያን ፊልም ስራዎችን በመግዛት በጣቢያዎች ለማቅረብ ውጥን ይዘዋል።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያን ባህል እና አኗኗር ለተቀረው ዓለም የሚያስተዋውቁ ስራዎችን በተለያዩ ጊዜያት በማዘጋጀት በተለያዩ የዲኤስቲቪ ጣቢያዎች እንዲያቀርብ በድርጅታቸው አማካኝነት ሲሰሩ ቆይተዋል።

በየጊዜው ከሚጨምረው የሳተላይቱ ተጠቃሚዎች ቁጥር እና ከሚያድገው ገቢው ባለፈ ግን በማህበራዊ አገልግሎቶችም በመሳተፍ የወይዘሮ ገሊላ ድርጅት የበኩሉን ሲወጣ መቆየቱን ይናገራሉ። በተለይ የፐላዝማ ቴሌቪዥን ስርጭት በየትምህርት ቤቶቹ በሚሰጥበት ወቅት የዲኤስቲቪ ስርጭት አካል ከሆኑት የናሽናል ጂኦግራፊ፣ የሳይንስ እና ሌሎች ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በፐላዝማ በነጻ ለተማሪዎች እንዲተላለፉ አድርጓል። በዚህም ተማሪዎች የተሻለ የሳይንስ እና አካባቢ እውቀት እንዲኖራቸው ጥረት መደረጉን ያስታውሳሉ።

ዲኤስቲቪ በአዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት እና የተለያዩ የስፖርት ውድድሮችን የቀጥታ ስርጭት ቀረጻ ሲከውንም ለተለያዩ የሀገር ውስጥ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ሰራተኞች ስለቀጥታ ስርጭት እና የቴክኒክ ስራዎች የተግባር ላይ ስልጠና እንዲሰጥ እድሉን ማመቻቸት መቻሉን ወይዘሮ ገሊላ ያስረዳሉ።

የወይዘሮ ገሊላ እና አጋራቸው ድርጅት አሁን ላይ የሳተላይት ስርጭቱን ገጠማ እና ቴክኒክ ስራ ከሚከውኑ ጊዜያዊ ሰራተኞቹ ባለፈ በቋሚነት 120 ሰራተኞችን ይዟል። በቀጣይ ጊዜያት ደግሞ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ውደድርን ገዝቶ ለማስተላለፍ የሚያስችል ፍላጎት መኖሩን እና ለዚህም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ያወጣውን ጨረታ ላይ ተሳትፎ እየተደረገ መሆኑን ያስረዳሉ።

ጨረታው የሚሳካ ከሆነ ደግሞ የኢትዮጵያን ስፖርት ለተቀረው ዓለም ከማስተላለፍ እና ቴክኒካዊ ድጋፎችን ከማድረግ በተጨማሪ በርካታ ሰራተኞችን ለመቅጠር የሚስችል እድል እንደሚፈጠር ተስፋ አድርገዋል።

ከአነስተኛ ካፒታል ምናልባትም ከጉልበት ወጪ ብቻ የተነሳው ካፒታላቸው አሁን ላይ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገቢ ላይ የደረሰው የወይዘሮ ገሊላ ድርጅት፤ በጠንካራ የጋራ ስራ እና የመምራት ብቃት የተገኘ መሆኑን የሚያውቋቸው ይመሰክራሉ።

ስራ ማለት ለእርሳቸው ዛሬም ጥረት ነገም ለለውጥ የሚደረግ ልፋት ያለበት ተግባር ነው። በዚህ መንገድ ማንኛውም ሰው በተሳተፈበት ዘርፍ በጥናት ላይ የተመሰረተ እና ውጤታማ ስራን ለማከናወን የሚጥር ከሆነ ለእራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሚተርፍ ንግድን መከወን ይቻላል የሚለው ደግሞ ምክራቸው ነው።

የደም ቧንቧ መስፋት በሽታ (ማቆር)

ሁለት አይነት የደም ቧንቧዎች አሉ።አካስጅን የተሸከሙና ደምን ከልብ ወደ ሌላው የሰውነት ክፍል የሚወስዱ የደም ቧንቧዎች አርተሪ ይባላሉ።ጥቅም ላይ የዋለውን ደም ከሌላው የሰውነት ክፍል ወደ ልብ የሚመልሱ ቧንቧዎች ደግሞ ቬን ይባላሉ፡፡

ደም መልሶችም ሆኑ ደም ቅዳ ቧንቧዎች በሁሉም የሰውነታችን ክፍሎች የሚገኙ ናቸው።ደም ቧንቧን እንደ አንድ ፕላስቲክ ቲዩብ ወስደን መሀል ላይ ቆርጠን ብናየው ግድግዳውን ማየት እንችላለን።ደም ቅዳ ቧንቧ ግድግዳው ወፍራም ነው።የውስጠኛው፣ መካከለኛውና የላይኛው ተብለው የሚከፋፈሉ ሶስት ክፍሎች አሉት።በሌላም በኩል ደም መልስ ቧንቧዎች ግድግዳቸው ቀጭን ነው።ለዚህ ይመስላል፣ ከደም ቧንቧ መስፋት ጋር ለተያያዙ የጤና ችግሮች የተጋለጡ የሚሆኑት፡፡

የደም ቧንቧ መስፋት ራሱን የቻለ በሽታ ነው ወይስ የሴሎች በሽታዎች ምልክት ነው?መንስኤውስ?

የደም ቧንቧ መስፋት (ማቆር) ራሱን የቻለ በሽታ ነው።ደም በታችኛው የሰውነት ክፍላችን ወይም ከእግራችን አካባቢ በፍጥነት ወደ ሳንባና ልብ መመለስ ሲገባው፣ ለረዥም ጊዜ እግራችን ውስጥ ከቆየ የደም ቧንቧውን እየለጠጠው እና እያሰፋው ይሄዳል።ቀላል የሆኑ በቆዳ ላይና ከቆዳ ስር ትናንሽ ሸንትርትር ነገሮች በተለይ ሴቶች ላይ በታፋና በእግር ጀርባ አካባቢ ይታያሉ።ከዚህ ተነስቶ ከእግራችን ጀርባ አረንጓዴ (ሰማያዊ) የሆኑ ትላልቅ እብጠቶችን የሚያመጡ የደም ቧንቧዎች መቋጠር ይታያል።ይህ ችግር ገፍቶ ከፍተኛ ደረጃ በሚደርስበት ጊዜ አልሰር እስከ መፍጠር እንዲሁም የእግሮቻችንን ከለር እስከ መቀየር ሊደርስ ይችላል።በደም ቧንቧ መስፋት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፡፡

መንስኤዎች

የደም ቧንቧ መስፋት የራሱ የሆኑ መንስኤዎች ያሉት በሽታ ነው።ከመንስኤዎቹ አንፃር ዋና ዋና የምንላቸውን

– ደም መልስ ቧንቧዎች ደምን ወደ ታችኛው የአካል ክፍል እንዳይመለስ የሚያደርጉ ቫልቮች አሏቸው።እነዚህ ቫልቮች ብዙውን ጊዜ በተፈጥሮ አለመኖር፣

– ደምን ወደታችኛው የአካል ክፍል እንዳይመለስ የሚያደርጉ ቫልቮች በተፈጥሮ ደካማ በሚሆኑበት ጊዜ፤

– ለረዥም ጊዜ ቁሞ መስራት ደም እግራችን አካባቢ ለረዥም ጊዜ እንዲቆይ ስለሚያደርገው ደም መልስ ቧንቧዎች እየተለጠጡ ይሄዳሉ፤

– በእርግዝና ወቅት የተለያዩ አካላዊና የሆርሞን ለውጦች ይከሰታሉ።በዚህ ምክንያት በእርግዝና ወቅት የደም ቧንቧ መለጠጥ ይከሰታል፤


– ለረዥም ጊዜ የቆየ ጉበት በሽታ የደም ቧንቧ መስፋትን ያመጣል፤

– የፊንጢጣ ኪንታሮት፡፡

የደም መስፋት በሽታ ምልክቶች

የደም ቧንቧ መስፋት ብዙ ምልክቶችን አያሳይም።ነገር ግን ችግሩ እየጨመረ ሲመጣ ለረዥም ሰዓት በሚቆምበት ጊዜ የተወሰኑ ምልክቶችን ያሳያል፡፡

– ከፍተኛ የእግር ህመም ስሜት፤



– እብጠት፤

– ውሃ መጠራቀም ይከሰታል፤

– በተለይ ሴቶች ላይ በመቀመጫና በእግር ጀርባ አካባቢ ሸንተረር የመሰሉ ነገሮች በብዛት ይታያሉ፡፡

– የቆዳ ከለሩ ስለሚቀየር ለእይታ የሚማርክ አይሆንም፤

– ችግሩ መፍትሄ ካልተሰጠውና እየቆየ የሚሄድ ከሆነ እግር አካባቢ አልሰር ይፈጥራል፡፡

– የቆዳ ቀለም መቹኮርኮር

– የደም ዝውውር መስተጓጎል

– የተለያዩ ቁስሎች ሲፈጠሩ አለመዳን

– የቆዳ መብለጭለጭ

የደም ቧንቧ ጥበት በሽታ ራሱን የቻለ አራት ደረጃዎች አሉት።ደረጃቸውን ቀለል ባለ መልኩ ለመግለፅ የጤና ችግሩ እያለ ምንም አይነት ምልክት ሳይኖር ሐኪሙ ብቻ ሲመረምር የሚያገኘው ከሆነ ደረጃ አንድ እንለዋለን።በሽታው ደረጃ ሁለት ላይ ከደረሰ በእንቅስቃሴ ወቅት ብቻ እግራችንን የህመም ስሜት የሚሰማን ይሆናል።ሶስተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚባለው፤ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ሳይኖር በዕረፍት ላይ ሁነን የህመም ስሜት መሰማት ከጀመረ አስጊ ሊባል የሚችል ደረጃ ላይ መድረሱን ያመላክታል።ከዚህ ከፍ ሲልም እግር ላይ ቁስለት ሊፈጥር ይችላል።እዚህ ከደረሰ የከፋ የሚባል ደረጃ ላይ መድረሱን ያሳያል፡፡

የደም ቧንቧ መስፋት (ማቆር) ምርመራ

በሽታው መከሰቱን ለማወቅ ምንም የሚያስቸግር ነገር የለም።ምክንያቱም ደም መልስ የሚባሉ የደም ቧንቧዎች ከውጭ በግልፅ የሚታዩ በመሆኑ በዓይናችን በማየት ብቻ ማረጋገጥ እንችላለን።ለደም ቧንቧ መስፋት ምንም አይነት የማረጋገጫ ምርመራ ማድረግ የሚያስፈልገው አይደለም።

በሕክምና ያስው መፍትሄው

የደም ቧንቧ መስፋትን እያንዳንዱ ሰው በቤቱ ውስጥ ሊያደርገው የሚገባ መፍትሄ ይኖራል።ለምሳሌ ለረዥም ሰዓት አለመቆም፣ ስራ መስራት ካለብን ቶሎ ቶሎ እየተቀመጡ እረፍትን ልምድ ማድረግና ስንቀመጥ እግራችንን ከፍ አድርገን መቀመጥ ጠቃሚ ይሆናል።ከዚህ በተጨማሪ ወፈር ያሉ ስቶኪንጎችን በመጠቀም፣ የሰፋውን የደም ቧንቧ ጨምቀው እንዲይዙትና ደም እንዳያቁር ማድረግ ይቻላል።በእነዚህ ሁኔታዎች የማይመለስ ከሆነ፣ በህክምናው ያለው የመፍትሄ አማራጭ በቀዶ ህክምና የሰፋውን የደም ቧንቧ ቆርጦ ማውጣት ብቻ ነው፡፡

የደም ቧንቧ መስፋት በወቅቱ ካልታከመ የሚያስከትለው ጉዳት

የማይድን አልሰር ወይም ሰፊ ቁስል ይፈጥራል። የተፈጠረው ቁስል የማያቋርጥ ስቃይ ያመጣል። መራመድን መከልከልና የእግር ውበትን ይቀንሳል። በተጨማሪም ጫማ አድርጎ ለመጓዝ ያስቸግራል።በመጨረሻም የአጥንት ኢንፌክሽን ያመጣል።

መከላከያ ዘዴ

ህብረተሰቡ ስለደም ቧንቧ መስፋት (ማቆር) በሽታ መኖሩንና ችግሩ በቀላሉ ሊታይ የሚችል እንዳልሆነ እንዲገነዘብ ማድረግ ያስፈልጋል።ከዚህ ውጭ የደም ቧንቧ መስፋትን ለመከላከል የሚያስችሉ ብዙ ነገሮች የሉም ማለት ይቻላል።ነገር ግን የባታችንን ጡንቻዎች የሚያጠነክሩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን መስራት በጣም ጠቃሚ ነው።አዘውትሮ በእግር መራመድ፣ በስራ ቦታ ብዙ ከመቀመጥና ከመቆም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መንቀሳቀስ ጠቃሚ ይሆናል።በስተመጨረሻ ሁሉም ሰው በእግር አካባቢ የህመም ሆነ የቆዳ ለውጦች ሲኖሩ በቀላሉ ማለፍ የለበትም።ሁልጊዜም የደም ቧንቧ መስፋትን ማሰብ ይኖርበታል፡፡

ምንጭ ፡- ዘ-ሀበሻ

በሽታ የመከላከል አቅምን እንዴት እንጨምር?

በሽታን ቀድሞ መከላከል ዋነኛው የህክምና ክፍል ነው። አንደኛው የመከላከያ መንገድ ደግሞ የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅምን መጨመር ነው። የትኞቹ ምግቦች ይህንን ሊያደርጉ እንደሚችሉ እናያለን።

በሽታ የመከላከል አቅምን የሚጨምሩ የምግብ አይነቶች የትኞቹ ናቸው?

አንዳንድ ምግቦችን በበቂ ሁኔታ መመገብ ለሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም እንደሚጨምሩ ብዙ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህን በማድረግም በቀላሉ ጉንፋን፣ ኢንፌክሽኖች እንዳይዙን ይከላከላሉ። በጥናት ከተረጋገጡ ምግቦች ጥቂቶቹን እናነሳ።

የሲትረስ ፍራፍሬ

ብዙ ሰዎች ጉንፋን ከያዛቸው በኋላ በሽታ የመከላከል አቅምን ለመጨመር በቫይታሚን ሲ የበለፀጉ ምግቦችን ያዘወትራሉ። ቫይታሚን ሲ ነጭ የደም ሴልን በመጨመር ከኢንፌክሽን ለመዋጋት ይረዳል።

ሁሉም የሲትረስ ፍራፍሬዎች በቫይታሚን ሲ የበለፀጉ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ፤ የወይን ፍሬ፣ ብርቱካን፣ መንደሪን፣ ሎሚ ይጠቀሳሉ። ሰውነታችን ቫይታሚን ሲን ስለማያስቀምጥ እለት ተእለት መወሰድ ይኖርበታል።

ቀይ የፈረንጅ ቃሪያ

ከሲትረስ ፍራፍሬዎች ቀይ የፈረንጅ ቃሪያ 3 ጊዜ የበለጠ የቫይታሚን ሲ መጠን ይይዛል። እንዲሁም በቤታ ካሮቲንም የበለፀገ ነው፤ ይህንንም ሰውነታችን ወደ ቫይታሚን ኤ በመቀየር የአይን እና የቆዳን ጤንነት ይጠብቃል። በሽታ የመከላከል አቅምን ከመጨመሩም ባሻገር ቫይታሚን ሲ ጤናማ ቆዳ እንዲኖር ያደርጋል።

አበባ ጎመን

አበባ ጎመን በቫታይሚን (ኤ፣ ሲ፣ ኢ)፣ ሚነራል፣ ፋይበር እና ሌሎች አንታይኢክሲዳንቶች የተሞላ የአትክልት አይነት ነው። ይህ አትክልት በጣም ጤናማ ከሚባሉት ይመደባል።

የጤና በረከቶቹን ላለማጣት የአበባ ጎመንን ብዙ ማብሰል አይመከርም። ጥናቶች እንደሚያሳዩት መቀቀልም የተሻለ እንደሆነ ነው።

ነጭ ሽንኩርት

ነጭ ሽንኩርት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚወደድ ነው። በስልጣኔዎች ውስጥ ነጭ ሽንኩርት በሽታን በመከላከሉ ዘርፍ ግንባር ቀደም ነበር። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ነጭ ሽንኩርት የደም ስር የመዘጋት ወይም የመጠጠር አቅምን ይቀንሳል።

ዝንጅብል

ዝንጅብል ከታመምን በኋላ የምንዞርበት ሌላው ጠቃሚ የምግብ አይነት ነው። የሰውነት መቆጣትን በመቀነስ የጉሮሮ መቁሰልን እና ኢንፌክሽንን ለመዋጋት ይረዳል። እንዲሁም የማቅለሽለሽ ስሜትንም ይቀንሳል።

በተጨማሪም ህመምን የመቀነስ፣ የደም ውስጥ ስብ መጠንን የመቀነስ ባህሪ አለው።

ቆስጣ

ቆስጣ ከቫይታሚን ሲ በተጨማሪ በብዙ አንታይኦክሲዳንቶች እና ብታ ካሮቲን የበለፀገ ነው። እነዚህም የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅምን ይጨምራል። ቆስጣም በውስጡ ያሉትን ንጥረነገሮችን እንዳያጣ ብዙ መብሰል የለበትም።

እርጎ

ማጣፈጫ ያልገባበት እርጎ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ይነገራል። እርጎ የቫይታሚን ዲ ምንጭ ነው። ቫይታሚን ዲ የሰውነትን በሽታ የመከላከል ስርዓት በማስተካከል በተፈጥሮአዊ መንገድ በሽታ የመከላከል አቅምን ይጨምራል።

እርድ

ይህ ቅመም የሰውነትን መቆጣትን ስለሚቀንስ ለአርትራይትስ በሽታ ለዓመታት ሰዎች ሲጠቀሙት ይታያል፤ ውጤቱም አስደናቂ ነው። እርድ በውስጡ በከፍተኛ መጠን ኩርኩሚን (Curcumin) የተባለ ንጥረ ነገር ይይዛል፤ ይህም ቀለሙ ቢጫ እንዲሆን እና በእንቅስቃሴ ምክንያት የሚመጣ የጡንቻ ጉዳትን እንደሚቀንስ ይነገራል። በተጨማሪም ንጥረ ነገሩ በጥናት የተረጋገጠ በሽታ የመከላከል አቅምን የመጨመር እና በቫይረስ የሚመጡ በሽታዎችን ለመቋቋም እንደሚረዳ አሳይተዋል።

አረንጓዴ ሻይ

አረንጓዴ እና ጥቁር ሻይ ፍላቮኖይድ (Flavonoid) በተባለ አንታኦክሲዳንት የተሞላ ነው። አረንጓዴ ሻይ ከጥቁር ሻይ በተሻለ ተጨማሪ ሌሎች ሀይለኛ አንታኦክሲዳንቶችንም በውስጡ ይይዛል። ይህም የሰውነትን በሽታ የመከላከል ስርዓት እንደሚያግዝ ይነገራል። እንዲሁም አረንጓዴ ሻይ L-theanine የተባለ አሚኖ አሲድ ምንጭ ነው፤ ይህም ጀርምን ለመዋጋት የሚያስፈልግ ውህድን በመጨመር ሰውነትን እንደሚያግዝ ይነገራል።


ፓፓዬ

ፓፓዬ ሌላው በቫይታሚን ሲ የበለፀገ ፍራፍሬ ነው። በተጨማሪም ፓፓዬ የምግብ መፍጨት ስርዓትን የሚያሳልጥ እና ሴሎችን መቆጣት የሚቀንስ ውህድ አለው።ፓፓዬ በውስጡ ፖታሺየም፣ ማግኒዢየም እና ፎሌት ስለሚይዝ ለጤና እጅጉን ጠቃሚ ነው።

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ
አስኪያጅ
ስልክ - 011-126-42-22
ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40
ምክትል ዋና አዘጋጅ
አስማኤል አረቦ
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-43-26
ኢሜል - ismaelarebo2011@gmail.com
አዘጋጆች
ማህሌት አብዱል
ቦጋለ አበበ
ክፍስዮሐንስ አንበርብር
ጌትነት ተስፋማርያም
መልካምስራ አፈወርቅ
ዋስልኝ አየለ
አምደኞች
ጌታቸው በስጠ/ዳግላስ ጴጥሮስ
አሸናፊ ዘደቡብ
ፍሬው አበበ
ቀምላችው አበበ
የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - epapromotion@press.et
ስልክ - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-156-98-62
የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ - 011-156-98-65
የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39
ማከፋፈያ
ስልክ - 011-157-02-70

ርዕሰ አንቀፅ

ጊዜው አልረፈደም!



በሀገራችን የቅርቡም ሆነ የሩቁ የፖለቲካ ታሪካችን የግለሰቦች የፖለቲካ ተሳትፎ አልፋ እና አሜጋ የመሆኑ ባህል በስፋት የሚንጸባረቅበት ነው። በሆነ አጋጣሚ ወደ ስልጣን የመጡ ግለሰቦችም ሆኑ የግለሰብ ስብስቦች /ቡድኖች / ወደ ስልጣን በቀረቡ ቁጥር ድንገት ሰው የመሆናቸው ፍጥረታዊ ስብዕናቸው እየጠፋ ጣኦት ወደ መሆን የሚሄዱበትን እውነታ ታሪኮቻችንና አደባባዮቻችን በየዘመኑ የታዘቡት እና የታዘቡት እውነታ ነው።

በቅርቡ ካለው የሀገራችን መሪዎች ታሪክ ተነስተን ንጉሳዊውንና በደም ሀረግ ላይ የተንጠላጠለውን አገዛዝ ብንመለከት፤ የደም ሀረጉን የተከተለ ከሰውነት ያለፈ ሰውነት ተሰጥቶት እንደነበረ የአደባባይ ሚስጢር ነው። የአገዛዙ መሰረት የነበሩ ግለሰቦች ሳይቀሩ ራሳቸውን እንደ ትናንሽ ጣኦት አድርገው የማየቱ እውነታም የተለመደ ነበር።

ከራሳቸው እና ራሳቸው ፈቃድ ባለፈ ህዝቡ የራሱ ፈቃድ የሌለው የስርዓቱ ተናጋሪ እቃ አድርጎ የማየት የገዘፈ ማንነት ነበራቸው። ይህ ያልተገባ የተሳሳተ የስብዕና ግንባታቸው ሀገርና ህዝብን የቱን ያህል ወድ ዋጋ እንዳስከፈለ ብዙ ለመናገር መድፈር አያስፈልግም። የአደባባይ ሚስጥር ነውና።

የአገዛዙን ውድቀት ተከትሎ በተጨናገፈው አብዮት ወደ ስልጣን የመጣው የወታደራዊው ጁንታ ስብስብ በቀደመው መልኩ ራሱን ለመግለጽ ርዕዮተ ዓለማዊ መሰረት ባይኖረውም፤ ራሱን የተለየ የህዝብ ድምጽና በዕውቀት ባልተቃኘ ደመነፍሳዊ ስብዕና ራሱን የተለየ አድርጎ በመቁጠር ሐገርንና ህዝብን የቱን ያህል መራር ዋጋ እንዳስከፈለ ለየትኛውም ኢትዮጵያዊ የሚነገር አይደለም። ህዝብን የራሱ ፈቃድ የሌለው የአበዩቱ ዕቃ አድርጎ ሲመለከት ቆይቷል። በዚህም ተከታታይ ትውልዶችን የበረሀ ሲሳይ አድርጓል።

መላውን ሃገር የጦርነትና የእልቂት አውድማ በማድረግ በሀገራዊ ታሪክ ውስጥ በቀላሉ ሊጠፋ የማይችል ጠባሳዎችንም ጥሎ አልፏል። ይህ ጠባሳ በብዙዎች ስነ ልቦና ላይ ለወሬ የማይመች ቀውስ ፈጥሯል። በሃገራዊ ፖለቲካው ላይ ጥሎት ያለፈውም ድብልቅልቅ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

አሁን ተከትሎ በብዙ የደም መስዋዕት ወደስልጣን የመጣውና ለራሱ ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ የሚል የገዘፈ ስብዕና የሰጠው ህወሓት መራሹ በረሀኛው ቡድን ራሱን የሁሉ ነገር አልፋና አሜጋ አድርጎ በመቁጠር በብዙ መስዋዕትነት የተገኘውን የህዝቦች ድል ጠልፎ የመንደርና የቡድን ፍላጎት ማስፈጸሚያ በማድረግ የቱን ያህል ለትውልዶች የሚተርፍ ዋጋ ሀገርና ሕዝብን ማስከፈሉ ይታወቃል።

ይህ መንደርተኛ ቡድን ገና ከጅምሩ ለራሱ በነበረው ግምትና ከዚህ በሚመነጭ ባህሪ በፈጠረው የመፋነን ስነልቦና ራሱን የሁሉ ነገር አድራጊና ፈጣሪ አድርጎ እንዲያይ አድርጎታል። የከፋው ደግሞ የራሱን ዘመን የማይሻገር የጠራ የአስተሳሰብ መሰረት የሌለው፣ ቅንጥብጣቢ መልክና ቅርጽ የሌለውን፤ ማህበረሰብ ነክ ያረጀና ያፈጀ አስተሳብ በቀደመው ዘመን መንፈስ በህዝቦች ላይ ጭኗል። ለዚህም ህዝባችን የከፈለው ዋጋ በቀደመው ዘመን ከተከፈለው የተናነሰ አይደለም ።

ለራሳቸውና ለህዝባቸው የተሻለ ዘመንን በመሻት የህይወት ዋጋ በከፈሉ ዜጎቻችን ደም ራሳቸውን ትናንሽ ጣኦታት አድርገው የሚያዩ በዚህ መሳታቸው ህዝብ የራሱን እጣ ፋንታ መወሰን የማይችል ያልበቃ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ እሴት የታከለበት ሸቀጥ አድርገው የሚያምኑ፤ በዚህም አስተሳሰባቸው የህዝቡን ህይወት የፖለቲካ ገበያ ሸቀጥ አድርገው እንዲያስቡ ሆነዋል ።

ለነሱ የተሳሳተ አስተሳሰብ በነጻነት ስም በሀገሪቱ ተራሮችና ሸንተረሮች ባስገበሩት የንጹህን ደም ራሳቸውን አልፋና አሜጋ አድርገው ባልተገባ መልኩ ራሱን፣ ልጆቹን የልጅ ልጆቹንም ጭምር በገበረው ህዝብ ላይ ሲፋንኑ ቆይተዋል። በተስፋው ላይ ሲያመነዝሩና ሲሳለቁ ዓመታትን አስቆጥረዋል ።

እነዚህ መንደርተኛ ቡድኖች ዛሬ ላይ ለለመዱት የደም ግብር በተስፋው ሲሳለቁበትና በስሙ ሲነግዱበት የነበረውን የትግራይ ህዝብ እንደ ትናንቱ የመስዋዕት በግ አድርገው፣ የበሰበሰውንና እንኳን የትግራይን ህዝብ መላውን ሀገር በዘመናት መካከል ትልቅ ዋጋ ያስከፈለውን አስተሳሰብ ለመዋጀት እላይ ታች እያሉ ነው። አሁኑም በንጹህን ደም ወደሚቀጥለው ዘመን ለመሻገር ዓይናቸውን በጨው አሽተው አደባባዮችን ሞልተዋል።

እነዚህን ራሳቸውን ትናንሽ ጣኦታት አድርገው የሚያስቡ ሕዝብን ከመንጋነት ባለፈ የራሱን እጣ ፋንታ ለመቅረጽ አቅምም ሆነ ብቃት የለውም ብለው የሚያምኑ፤ ለህዝብና ለህዝብ ፍቃድ በንቀት የተሞሉ፤ በተደራጀ ሴራ ራሳቸውን ከፍታ ላይ ያስቀመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች ሰው መሆናቸው ከሰውም በላይ በተፈጥሮ ህግ መሰረት ያረጁና ትውልዱን የመወከል አቅምና ብቃት እንደሌላቸው ሁሉም አደባባይ ወጥቶ ሊነግራቸው ይገባል።

በተለይም በቀደመው ዘመን በተስፋው ያመነዘሩበት ፤ ልጆቹን ለተስፋው መርቆ በአደራ ጭምር የሠጣቸውን የልጆቹን የመስዋእትነት ተስፋ በአደባባይ የበሉ፤ ዛሬም ያለአንዳች አፍረት ልጆቹን የመስዋዕት ዕቃ አድርገው በማቅረብ ለጡረተኛ ህይወታቸው ተስፋ ለማድረግ የሚጥሩትን ቢቃቸሁ፤ ሰዎች ናችሁ ፤ እረፉ ትውልዱ እጣ ፋንታውን ለመቅረጽ የበቃ ትውልዳዊ ማንነት አለው ሊላቸው ይገባል።

እነዚህን ራሳቸውን ትናንሽ ጣኦት አድርገው አምልኮ የሚሹ የሀገር እና የህዝብ ሸክሞች ከሸክም አልፈው እርግማን እንዳይሆኑ ከላዩ ላይ አርቆ ሊጥላቸው ይገባል። በነጻነትም በራሱ እጣ ፈንታ ላይ የመወሰን ሰብአዊ መብቱን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል። ለእነዚህ በደም ግብር ዘመናቸውን ለመዋጀት ለሚፈልጉ ሀይሎች ዘመኑ እንደ ቀደመው ዘመን በደም ግብር የሚሸጋገሩበት እንዳልሆነ በተግባር በእንቢተኝነት ሊነግራቸው ይገባል። በቀደመው ዘመን ባስገበሩት የንጹህን ደም የተዋጀውን ችግር መቅረፍ የአሁኑ ትውልድ ወቅታዊ አጀንዳ መሆኑንም በሚገባቸው ቋንቋ ሊነግራቸው ያስፈልጋል፤ ለዚህ ደግሞ ጊዜው አልረፈደም!

ከእናንተም ከእኛም

የዓርባ ስልሳ ዓርባ ጣጣዎች

መ.ኃ

ሰው ለመኖር ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ ያስፈልገዋል የሚለው ከሳይንስ ባለፈ በገሃዱ ዓለም የሚታየው አልፎ አልፎ ነው። ያለመጠለያ ዘመናትን የሚባትሉና የሰማይ ያህል የራቃቸው ዜጎች ብዛት ቤት ይቁጠረው። ቤት ከመሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱ እንደሆነ ፊደል መቁጠጥ ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ ያወቅነው የነቢብ ሃቅ ቢሆንም ዛሬ ላይ በንልማሳ ዕድሜ ጭምር በነቢብ የቆጠርነውን ቤት ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዱ ነው የሚለውን ብሂል በተግባር ኖረንበት ያረጋገጥነው እጅግ ጥቂት ዕድለኖች ነን።

የዜጎች ጥረት ታክሎበት ለዜጎች በተመጣጣኝ ዋጋ መጠለያ ቤት የማቅረቡ ኃላፊነት የመንግሥትም ጭምር ነው።አምና በየካቲት ወር የ40/60 እና የ20/80 ቤቶች ዕጣ እንደሚወጣ እና ይህም በመገናኛ ብዙኃን እንደሚተላለፍ ተነግሮ ተላልፏል።ይህም የመንግሥትን ከፍተኛ ኃላፊነት ከሚያሳዩ መገለጫዎች አንዱ ነው።

የካቲት 27 ቀን 2011 ዓ.ም ዕጣው ይውጣ እንጂ ቤቶቹ ከ18 ወራት በኋላ ዛሬም ለባለቤቶች መተላለፍ አልቻሉም። በመጀመሪያ 100% የቤቱን ዋጋ የቆጠብን እያለን 40 ብቻ ለቆጠቡ እንዴት ይወጣል ያሉ ግለሰቦች ከሰሱ፣ ቤቶቹም ታገዱ ተባለ። እግዱ ወዲያውኑ በፍርድ ቤት ቢነሳም ቤቶቹ ግን አልተላለፉም።ያም ባይሆን ቤቶቹ ሳይጠናቀቁ ዕጣ እየወጣባቸው እንደሆነ መታወቅ አለበት።

በጋዜጣችሁ አዲስ ዘመን ማክሰኞ ነሐሴ 12 ቀን 2012 ዓ.ም ዕትም በከተሜነት ዐምድ ሥር የተጠቀሰው ከቸግሩ እጅግ በጣም ጥቂቱ ነው።በጽሑፉ ርዕስ እንደተጠቀሰው የመረጃ ግልጽነት ማጣት ከሁለተኛ ዙር 40/60 የማስተላለፍ ሒደት አንዱ ነው። ብቸኛው ግን አይደለም።

ዕጣው ሲወጣ የቤት ቁጥር ቀርቶ የፎቁ ቁጥር አልነበረም። ከወራት በኋላ ይህ ሲሟላም በአንድ ቦታ እየተደረገ ያለ ግንባታ በተቀራራቢ ደረጃ በሌላ ቦታ አልተደረገም። ባንድ የግንባታ ስፍራ የተሟላው በሌላ ሥፍራ/ሳይት/ አልተሟላም።

በምሕረት ሞገስ ጽሑፍ እንደተጠቀሰው ሁሉም የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ሠራተኞች ቤቶቹ የት እንደሚገኙ ማወቅ ባይጠበቅባቸውም የግንባታው ደረጃ ከምን እንደደረሰ ቢያንስ ውስን ባለሙያዎች እና ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቶች ማወቅ አለባቸው። ተቋሙ አሰሪ እንደመሆኑ የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ በትክክል ቢተገብር አብዛኞቹ ችግሮች በተቃለሉ። አማካሪ ድርጅትም የተዛነፈ ነገር ሲያይ (ድርጅቱ ካለ) ማስተካከል የወግ ነበር።

ይህ ባለመሆኑም አሳንሰር እና ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ (garbage shooter) በተለይም የፍሳሽ ቆሻሻ፣ የውሃ እና ኤሌክትሪክ መስመር ሳይሟላ ለቁልፍ ርክክብ" መጣደፍ ባልተገባ ነበር።ቁልፍ ርክክብ ይባል እንጂ በየቤቱ ሲኬድ በር እንጂ ቁልፍ በሌለበት ቁልፍ ርክክብ ማለት ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነው። ጥቂት በማይባሉ ቦታዎች ደግሞ በሮችም የለም።

ቁልፍ መረካከቢያ ሰነዱም ሲታይ ሳይሟሉ ተሟልተዋል በተባሉ ቁሳቁስ ቴክኒካዊ ስም የተሞላ ነው- ሌላ ግልጽነት መጉደል።

በዚህም ላይ ተጠያቂነት ባለመዘርጋቱ የማጠናቀቂያ ሥራ እኔ ልሥራ ብሎ ሕንጻ ተቋራጭ በአቋራጭ በመምጣትም ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ መሆኑን የአዲስ ዘመን የምርመራ ጋዜጠኞች ሊያረጋግጡ ይችላሉ። ብዕሪ መንገዳቸውንም ለኮንትራክተር ስለሚጨነቁ "ደጋግ" ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ሠራተኞችም ይነግሩናል። በዚህ በኩል ግብዐት ከመንግሥት እየቀረበ በዚያ በኩል ሥራውን ባልተሟላ ጥራት ሠርቶ ከፈሉኝ እኔ ላጠናቅ መገፋፋት ሙስና እንጂ ለቤት ባለቤት ማዘን አይደለም።

ሁሉም ተቋራጮች እንዲህ ይሠራሉ ማለት አይደለም። ሥራቸውን በዐይን አይቶ እንኳን ባለቤት መንገደኛም የሚያመሠግናቸው አሉ። በሌላ በኩል ግን ለምሳሌ በቦሌ ቡልቡላ እንደሆነው አንዱ ሊጠናቅ የደረሰ ሌላው ጭራሽ ያልተጀመረ የሚመስል አለ።በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ ፕሮጀክት መሐንዲሶች እና ሥራ አስኪያጆች እንዲሁም አማካሪዎች ምን እየሠራህ ነው? ለምን አልሠራህም? ማለት የሚችሉት- እስካሁን ያሉ አይመሥልም እንጂ!

ቤት በሀገሬ ይኑረኝ ብሎ/ብላ በዶላር ከምዕራብ ሀገራት የቆጠቡትም፣ በቤት ኪራይ የተማረሩ የመንግሥት ሠራተኞችም ሆኑ በአረብ ሀገራት በቤት ሠራተኝነት ደም እንባ እየተፉ ያሉ እህቶቻችን ቤት በዚህ መልኩ እየተወዛወዘ ነው። መንግሥት ዜጎች መኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው አሁንም አዳዲስ ግንባታ እየገነባ ቢሆንም አምና የወጡት የዐርባ ስልሳ ቤቶች ግን ቁልፍ ርክክብ ቢደረግባቸውም ጨርሶ ለአርባ በመቶ እና ከዚያ በላይ ቆጣቢዎች ባለመሠጠታቸው ሥራቸው ውሃ እየተኛ፣ ውስጣቸው ሕገወጥ ነዋሪ ቤቱ ብሎ እየተኛ ነው። ከዓመት በፊት ዕጣ የወጣባቸው ቤቶችን ባለቤቶች የሚኖሩባቸው መቼ ነው የሚለው ጥያቄ አልመለሰም። መመለስ ያለበት አካል እንቶኔን ጠይቁ ይላል ከቤት ባለቤቶቹ እንደተረዳነው::

ይህን የሕዝብ ጥያቄ አስመልክቶ ነሐሴ 19 ቀን 2012 ዓ.ም በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ቢዘገይም የቤቶች ልማት ኤጀንሲ ምላሽ መስጠቱ የሚያስጨበጭበለት ነው።ነገር ግን የሥራ ኃላፊው በምላሻቸው እንዳሉት ለቤት ባለቤቶች ተደውሎ ኑ ተዋዋሉ ኑ ቁልፍ ተረከቡ አልተባለም።ኤጀንሲው ለእያንዳንዱ ደውያለሁ ቢልም የተደረገው ግን ቦሌ ክፍለ ከተማ ግቢ ለዚያውም በግልጽ በማይታይ ቦታ ነው እስካሁን ያለው የተለጠፈው። በእርግጥ ግለሰቦቹ የ40/60 ባለቤቶች በራሳቸው ጥረት በቴሌግራም እና በፌስቡክ ማስታወቂያው የበለጠ ተደራሽ እንዲሆን አድርገዋል::

የዛሬ ሰባት ዓመት ለ40/60 ቤቶች ግንባታ ሲጀመር በአንድ ዓመት ተኩል ግፋ ቢል በሁለት እና በሦስት ዓመት ተጠናቆ ለባለ ዕድል እንደሚተላለፍ ነበር። ሆኖም ከሸገርን ማስዋብ እና መሰል ፕሮጀክቶች ልምድ ያልቀሰመው ተቋም እና አሠራር እስከ አሁን ማለትም ከሰባት ዓመት በኋላም አልተጠናቀቀም።በአሁን አያያዙም በአንድ እና በሁለት ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ አይመሥልም። ለዚህም ነው የቤቶቹ ምዝገባ ሲካሔድ 275 ሺህ ብር የተተመነለት ባለ ሁለት መኝታ ቤት አምና በቤቶቹ ላይ ውል መዋዋል ሲጀመር በ182 በመቶ ጨምሮ 499ሺህ ብር የሆነው። አሁንም ቶሎ ካልተጠናቀቀ አጠቃላይ ወጪው እየጨመረ እንደሚሔድ (የቁሳቁስ በየጊዜው መናር እንዳለ ሆኖ) ለማወቅ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ መሆን አይጠበቅም። የመንግሥት እና የግለሰቦች ሀብት ቶሎ ባለመሥራት ብቻ ምን ያህል እንደሚባክን ከዚህ የበለጠ ምን ማሳያ ማቅረብ ይቻላል?

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ አስተያየታቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሑፎች የዝግጅት ክፍሱን አቋም አያመለክቱም።

ህይወት ፈርጅ ብዙ ገጽታዎች አሏትመውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ደኖራልከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላልአግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል።ይህ የህይወት እውነታ ነውበጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉየህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉበከፍታ ውስጥ የሚገኙት €€እንዲህም ይኖራል እንዴ?« ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉለተቸገሩት ያዘናሉካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉበተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉበመሆኑም €€እንዲህም ይኖራል« ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

በአራት አካል ጉዳተኛ ልጆች የተፈተነ የቤተሰብ ሕይወት

ክፍለዮሐንስ አንበርብር





ሙሉ ለሙሉ ማሳከም አልቻልንም ያለንን ሀብትና በሕይወታችን የሰበሰብናትን ጥሪት ጨርሰናልና። አሁን ያለን ተስፋ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት መማፀንና እገዛ መፈለግ ነው

ጉራጌ ዞን

አቶ አወል ዑመር 57 ዓመት ሞልቷቸዋል። ከትዳር አጋራቸው ጋር ጉራጌ ዞን በእዣ ወረዳ አጓጅ ተረህ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። አቶ አወል ዑመር እና ባለቤታቸው ወይዘሮ ዓለም በአገሬው ባህል መሠረት ትዳር ሲመሰርቱ «ወልዶ ለመሣም ዘርቶ ለመቃም» ያብቃችሁ ተብለው በአገሬው ባህል መሠረት ተመረቁ። በመጀመሪያም ሴት ልጅ ወለዱ። ደስም ተሰኙ። ቆይተው ለሴት ልጃቸው ወንድም ወይንም እህት ያስፈልጋል ብለው ልጅ ዳግም ወለዱ። ግን በ1980 ዓ.ም ሁለተኛ ልጃቸው አብዲልአህሚድ አወል ጤናማ መሆን የቻለው እስከ ዘጠነኛው ወር ብቻ ነበር። ገና ህመሙ ሲጀምረው አካባቢ ተቅማጥ ያዘወትርበት ነበር። በሂደትም እጁ አልታዘዝ አለው። ቀስ በቀስ ደግሞ ሌላ አካሉንም ማንቀሳቀስ ከበደው። ታዲያ እስካሁንም በሰው እገዛ መንቀሳቀስ ግድ ሆነበት። በሆነው ነገር ባልና ሚስት ተደናገጡ። ግን የፈጣሪ ሥራ ነው ብለው አምላካቸውን ማማረር አልፈለጉም።

የአቶ አወል ቤተሰብ በልጃቸው ሁኔታ ተስፋ አልቆረጡም። ይልቁንም ሌላ ጤናማ ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ፈጣሪን በማመፀን ባጢል የተባለ ልጅ ደግሞ በ1982 ዓ.ም ወለዱ። ይሁንና የተወለደው ልጅ ስምንት ወር ሲሞላው የህመም ምልክቶችን ማሳየት ጀመረ። ህመሙ ከመጀመሪያ ልጃቸው ህመም ጋር ተመሳሳይ ሆነ። በሆነው ነገር ባልና ሚስት እጅግ ተደናገጡ። ከጥቂት ዓመታት በኋላም ልጅ ለመውለድ ወሰኑ። አራት ተከታታይ ልጆችን ወለዱ። እነዚህ ሁለት ልጆች ግን የጤና እክል አልገጠማቸውም።

ከእነዚህ ልጆች በኋላ ደግሞ 1994 ዓ.ም ፈይሰል የሚባል ልጅ ተወለደ። ይህም ልጅ በስምንተኛ ወር ታመመ። በሁኔታው ግራ ተጋብተው ልጆቻቸውን ለማሳደግ ጥረታቸውን ጀመሩ አቶ አወልና የትዳር አጋራቸው። ከአሁን በኋላ ልጅ መውለድ በቃን ብለው ተስማሙ። ግን 1999 ደግሞ ሳያት ተወለደች። እርሷም በተመሣሣይ መንገድ እንደ ወንድሞቿ ታመመች።

ፍሬ አልባ ልፋት

አቶ አወል የልጆቻቸውን ጤና እክል ለመታደግ አለ የተባለ የባህል ሐኪም ሁሉ ሞክረዋል። አንድም ሳይሰስቱ ሀብትና ንብረት ጨርሰው ለማሳከም ጥረት አድርገዋል። የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ድረስ ሕክምና ሞክረው ጥሪታቸውን አሟጠው ተጠቅመመል። ግን ምንም ፍንጭ አጡ። ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ተጫናቸው። ከባለቤታቸው ጋር በተራ ሆነው ከእነዚህ ልጆች አብሮ መዋል፣ ማሳደጉ ግድ ሆነ። ታዲያ ከዘጠኝ የአብራካቸው ክፋይ ውስጥ አራት ልጆቻቸው የአልጋ ቁራኛ ሆነው ከቤት ዋሉ። እንደ እኩዮቻቸው የፊደል ገበታ ለመቁደስ ሳይታደሉ ቀሩ። ቤተሰብም እነዚህን ልጆች ለማሳደግና ለማኖር ፍዳ ማየት ሆነ።

አቶ አወል ከወለዷቸው ዘጠኝ ልጆች ውስጥ የመጀመሪያ ልጃቸው ከ10ኛ ክፍል ትምህርት አቋረጠች። ሁለት ወንዶች ደግሞ 10ኛ ክፍል ቢደርሱም ውጤት አልመጣላቸውም። ታዲያ የቤታቸውን ችግር ለማቃለል አንደኛው ልጅ እዛው ገጠር አባቱን ማገዝ ጀመረ። አንደኛው ደግሞ ሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ መጣ። ሁለት ሴቶች ደግሞ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ተምረው ነበር። በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ራሳቸውን ለማኖርና ቤተሰብ ለማገዝ እየተፍጨረጨሩ ነው።

ትካዜ የዋጠው ሕይወት

አቶ አወል ዑመር ከባለቤታቸው ወይዘሮ ዓለም ጋር በሆኑት ነገሮች ሁሉ በጣም ስሜታቸውን እንደተነካ ይናገራሉ። የመጀመሪያው ችግር ሲፈጠር ተደናግጠው ነበር። ሁለተኛው ተመሳሳይ ችግር ሲገጥመን እጅግ አዝነዋል። ችግሩ ሲደጋገም ደግሞ ማህበረሰቡ የሚናገረውና ሁኔታዎች ሕመም ፈጠሩባቸው። በሆነብን ከባለቤቴ ጋር እየተከዝን ልባችን እንደ ተንገበገበ ዓይናችን እንባ እንዳቀረረ ይሸው ዛሬም አለን ይላሉ።

አቶ አወል የደረሰባቸውን የሥነ ልቦና ጫና ሲያስረዱ «ሰዎች አውርተው! አውርተው! ሲድከማቸው ትተውናል። አንዳንዶቹ ይህ በአንድ ቤት ውስጥ በተከታታይ ሲከሰት እጅግ የከፋ የአላህ ቁጣ ነው ይላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ይህ ከስተት የመጣው ከባዕድ አምልኮ ጋር በተያያዘ ነው» በማለት ነው የገለፁት።

ገሚሱ ደግሞ ይህ የሆነው ፈጣሪ ምክያት ስላለው ነው ስለዚህ ብዙም መጨነቅ አያስፈልግም እርሱ የፈቀደውና የወደደው ነው በማለት እንደሚያፅናኗቸው ያስረዳሉ፡ «እኔ እና ባለቤቴም የሰዎችን ወሬ ሰምተን! ሰምተን! ሰልችቶናል። ከምንም በላይ ግን የሚያሳስበን ልጆቻችን እንዲህ ሆነው መቅረታቸው ነው። እኛ ግን አሁን የገጠማቸው ችግር በፈጣሪ ዘንድም ሆነ በሕክምና መፍትሄ አለው ብለን እናምናለን። አንድ ቀን ሁሉም ተሽሏቸው እንደ እኩዮቻቸው ይጫወቱ ይሆናል» ይላሉ አቶ አወል- ሐዘን በተሞላው ስሜት።

ጥሪ ለኢትዮጵያ ሕዝብ

አቶ አወል እሳቸው እና ባለቤታቸው እነዚህን ልጆች እንደልባቸው መንቀሳቀስ የማይችሉ በመሆኑ ማስተማር አለመቻላቸውን ይገልፃሉ። እስከ መጨረሻው ድረስ የሚቻላቸውን ጥረት ማድረጋቸውን ጠቅሰው «ይሁንና ሙሉ ለሙሉ ማሳከም አልቻልንም ያለንን ሀብትና በሕይወታችን የሰበሰብናትን ጥሪት ጨርሰናልና። አሁን ያለን ተስፋ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት መማፀንና እገዛ መፈለግ ነው» ይላሉ። ልጆቻቸው ከእኩዮቻቸው ጋር ውለው የሚጫወቱበት፤ የሚማሩበት ብቻ እንደ ዕድሜ አቻዎቻቸው እንዲሆኑ የዘወትር ፀሎታቸውና የሕይወት ዘመን ምኞታቸው እንደሆነ ይናገራሉ። እባካችሁ ኢትዮጵያውያን፤ ስለ ልጆች አምላክ ብላችሁ የልጆቻችን ጤና ታደጉልን፤ የቤተሰባችንን ደስታ መልሱልን ሲሉ አቶ አወል ዑመር ይማፀናሉ።

ሐኪሞች ምን አሉ?

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የሪፈራል ሆስፒታል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ዶክተር አብድልሰመድ ወርቁ፤ ልጆቹን በአካል ሄደው ጎብኝተዋል። የአንድ ቤተሰብ አባል በሆኑት አራቱ ልጆች ላይ የተከሰተው ችግር ከዕድገት ውስንነት ጋር የተያያዘ ይመስላል። ከሴቷ ልጅ በስተቀር ሦስቱ ልጆች የመረዳት አቅማቸው የተሻለ ነው።

ወንዶቹ ላይ ያለው ችግር የነርቫቸው በሚገባ አለመስራትና ጡንቻቸው በአግባቡ አለመታዘዝ ነው። የእጃቸውና እግራቸው ጡንቻ ላሽቋል። ታዲያ ለዚህ የመጀመሪያ ሕክምና ፊዚዮትራፒ ማድረግ ነው። በሂደት ደግሞ ሌሎች የሕክምና ክትትል ማድረግ ግድ ይላል።

በሴቷ ላይ ያለው የዕድገት ውስንነት ደግሞ ከፍ ያለ መሆኑን ዶክተሩ ተናግረዋል። በጀርባዋ ላይ የህብለ ሠረሠር አጥንቷ ወደ ጎን እና ወደ ውጭ የመጉበጥ ችግር አለበት። ያለ ሰው ድጋፍ መንቀሳቀስ አትችልም። በአጠቃላይ የጡንቻ እና ነርቭ ችግር አለባት።

በሌላ መንገድ ደግሞ የተፈጠረው የጤና እክል ከቤተሰብ እየወረደ የመጣ ወይንም የጀነቲክስ ውርርስ ያለበት ይመስላል። በአጠቃላይ ግን ልጆቹ ላይ የተከሰተው ህመም ከዕድገት ውስንነት (ኦቲዝም) ጋር የተያያዘ ይመስላል።

ወንዶቹ ጡንቻቸው መኮማተር እና መቸንከር ባህሪ ስላለው ወደ ጤንነቱ ሙሉ ለሙሉ ባይመለሱም በሕክምና የጤና መሻሻል እንዲመጣ ማድረግ ይቻላል። የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲም የተቻለውን ጥረት እንደሚያደርግ ዶክተር አብዱልሰመድ ጠቁመዋል። ይህን ለማድረግም በኢትየጵያ ውስጥ ሕክምና የሚሰጡ ተቋማት እንዳሉና ለዚህ ርብርብ ማድረግ ከኢትዮጵያውያን የሚጠበቅ እንደሆነ ይናገራሉ።

ልጆቹ በልጅነታቸው ሕክምና ቢያገኙ የተሻለ ይሆን ነበር። ከትምህር ገበታ ላይ የሚሳተፉበት ዕድል መፍጠር ይቻል ነበር። ግን መሰል ችግሮች በእነዚህ ቤተሰብ ላይ ብቻ የሚከሰት ሳይሆን እንደ አገርም ብዙ ችግሮች ይኖራሉ። ግን መሰል ፈተናዎችን መፍትሄ እንዲሰጣቸው ከታሰበ እንደ አገር የፖሊሲ ክለሣ ማድረግ ተገቢ መሆኑንም ይጠቁማሉ።

ՀԱՅԿ ՀԱՅԱՍՏԱՆԻ ՀԱՄԱՐ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՄԱՍՆԱՎՈՐ ԿԱԶՄԱԿԵՐՊՈՒԹՅՈՒՆ

ՀՈՒՐԻ ՉԱՓԱԶԱՆՑ ՀԱՆՐԱՊԵՏՈՒԹՅԱՆ ՆԱԽԱԳԱՀ ՍԵՐԺ ՍԱՐԳՍՅԱՆԻՆ

ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՄԱՍՆԱՎՈՐ ԿԱԶՄԱԿԵՐՊՈՒԹՅՈՒՆԸ ՀԱՅՏՆԻ ՀԱՅ ԺՈՂՈՎՐԴԻ ՀԱՄԱՐ ՀԱՐԿԱՎՈՐ ԽՆԴԻՐՆԵՐԻ ՄԱՍԻՆ

Ինչպես հայտնի է, Հայաստանի Հանրապետության նախագահ Սերժ Սարգսյանի հրամանագրով Հայկական մասնավոր կազմակերպությունը հայտնի է դարձել որպես հայ ժողովրդի համար հարկավոր խնդիրների մասին: Հրամանագրի համաձայն՝ Հայկական մասնավոր կազմակերպությունը պետք է զբաղվի հայ ժողովրդի համար հարկավոր խնդիրների լուծմամբ

פרסום ראשון

ברכת שנה טובה

ראש העיר ומועצת העיר מאחלים לתושבי העיר ולכל עם ישראל שנה טובה ומתוקה

8002ם רעדמד מעמד הפעולות הרפואיות שבוצעו בין עמיחי לבין אשתו!



מאת עמיחי בן-דוד (צילום: אלבום פרטי)

fenotei971@gmail.com

בשבוע שעבר הגיעו לבית החולים "שערי צדק" בירושלים שני אחים, שהתלוננו על כאבים עזים בבטן. לאחר בדיקות שונות התברר כי שניהם סובלים מאותה מחלה נדירה, שמקורה בגנים. הרופאים מעריכים כי מדובר בתופעה חריגה ביותר, שכן הסיכוי לכך שאחים יפתחו את המחלה הוא אחד למיליון. האחים, שאינם מודעים לכך שהם קרובי משפחה, מתאשפזים כעת במחלקה הפנימית ומקבלים טיפול תרופתי.

ד"ר יעל כהן, מנהלת המחלקה הפנימית בבית החולים, אמרה כי "מדובר במקרה מיוחד במינו, שמצריך מעקב צמוד ובדיקות נוספות. אנחנו מנסים להבין האם יש קשר גנטי בין המחלה לבין העובדה שהאחים גדלו באותו בית". לדבריה, "חשוב לציין כי המחלה אינה מדבקת, ואין כל סכנה לסביבה הקרובה של החולים".

האחים, בני 34 ו-36, גדלו בכפר הסמוך לעיר, ועברו לפני כשנתיים לגור בירושלים. לפי בני משפחתם, הם לא ידעו על הקשר ביניהם עד לפני כחודשיים, כאשר נפגשו במקרה בחתונה של בן דוד משותף. "הם התחילו לדבר ולגלות שיש להם אותם תסמינים בדיוק, ואז הבינו שמשהו לא בסדר", סיפר בן משפחה. "זה היה רגע מטלטל, אבל גם מרגש, כי סוף סוף הבינו למה הם סובלים".

הרופאים מציינים כי הטיפול במחלה עשוי להימשך חודשים רבים, ויכלול שילוב של תרופות וניתוח במקרים מסוימים. "המטרה שלנו היא לא רק לרפא, אלא גם לשפר את איכות החיים של החולים", אמרה ד"ר כהן. "אנחנו מאמינים שבעזרת מעקב צמוד ושיתוף פעולה מלא מצד המטופלים, נוכל להגיע לתוצאות טובות".

האחים עצמם הביעו תקווה כי סיפורם יעזור לאחרים. "לא ידענו שאנחנו לא לבד, ושיש עוד אנשים שעוברים את אותו הדבר", אמר אחד מהם. "אנחנו מקווים שנוכל לעזור לאחרים להרגיש פחות בודדים". בית החולים הודיע כי בכוונתו להקים קבוצת תמיכה למשפחות שנתקלו במחלה נדירה זו, ובה יוכלו החולים לשתף זה את זה בחוויותיהם.

מדור חדש: "שכנים טובים" – סיפורי עזרה הדדית בשכונת הגבעה

מאת: רונית אלמוג

בשכונת הגבעה, שבה מתגוררות כ-1,200 משפחות, נולד השבוע יוזמה חדשה שמטרתה לחזק את הקשרים בין השכנים. היוזמה, שנקראת "שכנים טובים", כוללת קבוצת וואטסאפ, לוח מודעות בכניסה לבניין ומפגש חודשי בגן השכונתי. כבר ביום הראשון הצטרפו למיזם 87 דיירים, ועוד עשרות נוספות ממתינות לאישור.

את הרעיון הגה יואב שמיר, תושב השכונה מזה 12 שנה, שהרגיש שהשכנים שלו הפכו לזרים גמורים. "פעם הכרנו את כל מי שגר ברחוב, היום אני לא יודע אפילו איך קוראים לשכנה שמולי", הוא אומר. "רציתי ליצור מקום שבו אנשים יוכלו לבקש עזרה בלי להרגיש מביכים, ולהציע עזרה בלי לחכות שיבקשו".

לפי הכללים שנקבעו, כל בקשה תפורסם בקבוצה, ורק אחר כך יתואמו הפרטים בפרטי. הבקשות הראשונות שהגיעו היו צנועות: השאלת מקדחה, עזרה בהעברת רהיטים, והסעה לרופא. "אנחנו לא רוצים שזה יהפוך לשוק יד שנייה", מסבירה שמיר. "כל בקשה שלא קשורה לעזרה הדדית תוסר".

המפגש החודשי הראשון יתקיים ביום חמישי הקרוב בגן השכונתי, החל מהשעה 18:00. בין הנושאים שעל סדר היום: תכנון חגיגת שכונה לקראת החגים, ודיון בהקמת מחסן משותף לציוד. "אנחנו מקווים שמי שיש לו מקדחה שלא משתמש בה כל השנה, יוכל להשאיל אותה לשכן", אומר שמיר בחיוך.

מחסן משותף לציוד ומפגש חודשי בגן

מאת: רונית אלמוג

בשכונת הגבעה, שבה מתגוררות כ-1,200 משפחות, נולד השבוע יוזמה חדשה שמטרתה לחזק את הקשרים בין השכנים. היוזמה, שנקראת "שכנים טובים", כוללת קבוצת וואטסאפ, לוח מודעות בכניסה לבניין ומפגש חודשי בגן השכונתי. כבר ביום הראשון הצטרפו למיזם 87 דיירים, ועוד עשרות נוספות ממתינות לאישור.

את הרעיון הגה יואב שמיר, תושב השכונה מזה 12 שנה, שהרגיש שהשכנים שלו הפכו לזרים גמורים. "פעם הכרנו את כל מי שגר ברחוב, היום אני לא יודע אפילו איך קוראים לשכנה שמולי", הוא אומר. "רציתי ליצור מקום שבו אנשים יוכלו לבקש עזרה בלי להרגיש מביכים, ולהציע עזרה בלי לחכות שיבקשו".

לפי הכללים שנקבעו, כל בקשה תפורסם בקבוצה, ורק אחר כך יתואמו הפרטים בפרטי. הבקשות הראשונות שהגיעו היו צנועות: השאלת מקדחה, עזרה בהעברת רהיטים, והסעה לרופא. "אנחנו לא רוצים שזה יהפוך לשוק יד שנייה", מסבירה שמיר. "כל בקשה שלא קשורה לעזרה הדדית תוסר".

המפגש החודשי הראשון יתקיים ביום חמישי הקרוב בגן השכונתי, החל מהשעה 18:00. בין הנושאים שעל סדר היום: תכנון חגיגת שכונה לקראת החגים, ודיון בהקמת מחסן משותף לציוד. "אנחנו מקווים שמי שיש לו מקדחה שלא משתמש בה כל השנה, יוכל להשאיל אותה לשכן", אומר שמיר בחיוך.

የዋሊያዎቹ አሰልጣኝ አልባነትና ቀጣዩ የአሰልጣኝ ቅጥር

ቦጋለ አበበ



የአፍሪካ አገራት የተሰያዩ የማጣሪያ ጨዋታዎችን ስማድረግ እየተዘጋጁ ቢሆንም ዋልያዎቹ አስካሁን አሰልጣኝ አልባ ናቸው፤

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባለፈው ሳምንት ባደረገው ስብሰባ በአዲሱ የተጫዋቾች ዝውውር ደንብ ላይ ተወያይቷል። በስፖርት ቤተሰቡ ሲጠበቅ የነበረው የቀጣዩ የዋሊያዎቹ አሰልጣኝ ማንነት ጉዳይ ግን አጀንዳ ሆኖ ሳይቀርብ ቀርቷል። በዚህም ምክንያት አመራሮቹ ቦታውን ለአሰልጣኝ አብርሃም መልሰው ይሰጡታል? ወይስ ሌላ አሰልጣኝ ይመደባል? የሚለው ምላሽ ሳያገኝ ቀርቷል።

አሰልጣኝ አብርሃም መብራቱ ከዋሊያዎቹ ጋር ከሁለት ዓመታት በላይ በነበራቸው ቆይታ አስራ አራት ጨዋታዎችን አድርገዋል። ከነዚህ መካከል አራቱን በአሸናፊነት ሲወጡ፣ አምስቱን በአቻ ውጤት ደምድመዋል። ቀሪዎቹን አምስት ጨዋታዎች ደግሞ ሽንፈት አስተናግደውባቸዋል። አስራ አራተኛ ጨዋታቸውን ባለፈው ህዳር ባህርዳር ላይ ሲያደርጉ ጠንካራዋን ኮትዲቯርን ሁለት ለአንድ በሆነ ውጤት ማሸነፋቸውና ቡድኑ ላይ በየጊዜው እያሳዩት የመጡት ለውጥ ለተጨማሪ ጊዜ ከቡድኑ ጋር እንዲቆዩ ያስችላቸዋል የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ አሳድሮ ነበር። ያም ሆኖ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሳቢያ ፌዴሬሽኑ ካለፈው ሐምሌ ሰላሳ ጀምሮ የአሰልጣኙን ውል ለማራዘም ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል።

ከሁለት ሳምንት በፊት የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) የአገራት ቀጣይ የማጣሪያ ውድድር መርሃግብሮችን ይፋ ማድረጉን ተከትሎ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ወደ እንቅስቃሴ የሚመለስበት ጊዜና ሁኔታ አነጋጋሪ ሆኗል።የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን (ካፍ) ምንም እንኳ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጉዳይ መፍትሔ ባያገኝም፣ በ2013 ዓ.ም. ለሚያከናውነው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ለአባል አገሮች የውድድር መርሃግብር ባወጣው መሠረት ከጥቅምት 30 እስከ ኅዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ጨምሮ የየአገራቱ ብሔራዊ ቡድኖች የየምድቡ ሦስተኛና አራተኛ የማጣሪያ ጨዋታ የሚያከናውኑ ይሆናል።

ከመጋቢት 13 እስከ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ ደግሞ የየምድቡ አምስተኛና ስድስተኛ ጨዋታዎች እንደሚከናወኑ አሳውቋል። ይህ የአፍሪካ ዋንጫ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰትን ተከትሎ ውድድሮቹ በመቋረጣቸው ምክንያት ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ኮንትራት ከሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ በማቋረጡ ቡድኑ አሠልጣኝ የለውም። ይህም ፌዴሬሽኑ በቅርብ ቀናት ውስጥ ለብሔራዊ ቡድኑ አሰልጣኝ የመቅጠር ግዴታ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። የካፍ የማጣሪያ ውድድሮች የሚጀመሩበት ጊዜ አጭር እንደመሆኑ ፌዴሬሽኑ አዲስ አሰልጣኝ ይሾማል ወይስ አሰልጣኝ አብረሃም እንዲቀጥሉ ያደርጋል የሚሉ ጉዳዮች አነጋጋሪ ናቸው። ፌዴሬሽኑ የአገሪቱ እግር ኳስ በቆመበት በዚህ ወቅት አዲስ አሰልጣኝ መሾሙ ከተጫዋቾች ምልመላና ከዝግጅት ጊዜ እጥረት ጋር በተያያዘ ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል የሚናገሩ የስፖርት ቤተሰቦች አሰልጣኝ አብረሃም የማጣሪያ ውድድሮቹን እንደጀመሩ ቢጨርሱ የተሻለ እንደሚሆን አጥብቀው ሲከራከሩ ይስተዋላል። ለዚህም ቀደም ብሎ የነበረውን የቡድን ስብስብ ከሌሎች አሰልጣኞች በተሻለ ስለሚያውቁት አዲስ አሰልጣኝ መጥቶ አዲስ ቡድን ለማዋቀርና ከዝግጅት ጊዜ እጥረት ጋር በተያያዘ ያለውን ጫና በተሻለ ሊወጡ እንደሚችሉ እምነት አላቸው።

ፌዴሬሽኑ ምንም ያህል የስራ ሃላፊዎች በተለያዩ ዘመናት ቢቀይርም ከአሰልጣኝ ቅጥር ጋር በተያያዘ ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት እንደሌለው የሚጠቁሙ የስፖርቱ ቅርብ ሰዎች አሁንም ስህተቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ይናገራሉ። ለዚህም ያለፉት ታሪኮቹን በማሳት የሚከራከሩ ወገኖች አዲስ ሃሳብ እንጂ አዲስ አሰልጣኝ እንደማያስፈልግ ይመግታሉ።

ፌዴሬሽኑ የአሰልጣኝ ቅጥር የጀመረው ከ1946 ጀምሮ ነው። የመጀመሪያው ተቀጣሪ የውጭ አሰልጣኝ የሆነው አስትሪያዊው ጆርጅ ብራውን ነው። ብራውን ለሀገሩ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋችና አልጣኝ ሆኖ ሰርቷል። የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን ለማሰልጠን ከብራውን እስከ ቶም ሲይንትፊት ድረስ 38 የውጭ አሰልጣኝ ተፈራርቀዋል። አንዳቸውም ግን በኢትዮጵያ እግር ኳስ ላይ ምንም ለውጥ አላሳዩም። ሁሉም ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው ብሩንዲ ወይንም ታንዛንያን ያሸንፋሉ ጋና ወይም ናይጀርያ አለበለዚያ ግብጽን መርታት አይችሉም።

የመጀመሪያን የነጥብ ጨዋታ በ1948 ግብጽን ስንገጥም ጆርጅ ብራውን ነበር አሰልጣኙ።5ለ0 ተሸነፈ። ይሄ በሆነ ከ55 ዓመት በኋላ አሰልጣኝ የነበረው ኤኔራ በናይጀሪያ 4ለ0 ተሸነፈ። በነዚያ 55 ዓመትም ይሁን ከዚያ በኋላ የመጡ የውጭ አሰልጣኞች በተመሳሳይ ነገር ነበር የተባረሩት። እስከ አሰልጣኝ ቶም ሴንቲፌንት ድረስ ባለው የብሔራዊ ቡድኑ ታሪክ ከውጭ 38 አሰልጣኝ ሲቀጠር ከሀገር ውስጥ41 አሰልጣኞች ተቀጥረዋል።አዳሙ አለሙ፤ጸሀዬ ባህረ፤ሉቻኖ ቫሳሎ፤ታደሰ ወልዳረጋይ፤ሽፈራው አጎናፍር፤መንግስቱ ወርቁ፤ዶክተር ተስፋዬ ጥላሁን፤አስራት ሀይሌ፤ስዩም አባተ፤ጌታህን ንብረጊዮርጊስ፤አዳነ ሀይለየሱስ፤ጸጋዬ ደስታ፤ሰውነት ቢሻው ፤ መኩሪያ አሸብርና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው።ከ41 ውስጥ 13ቱ 2 እና ከሁለት ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ ብሔራዊ ቡድኑን ያሰለጠኑ ናቸው። ለ21ኛው አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ በእያንዳንዱ ጨዋታ አሰልጣኝ እየተባረረ በመተካቱ ማጣሪያው እስኪያልቅ 5 ያህል አሰልጣኞች ተተካክተዋል።አንዳንድ ጊዜ በየስድስት ወሩ አሰልጣኝ የሚቀያየርበት ጊዜም ነበር።በ1951 በዓመት አራት አሰልጣኝ ተቀያይሯል። በ1957 ኬርቴስ የተባለ ተቀጠረ፣ በሁለት ወሩም ተባረረ፤ፈረንሳ ሹስ ተተካ በአራት ወሩ ተባረረ።አርቢልቢል ተተካ በመጀመሪያው ጨዋታ እዚህ በሞሮኮ ሲሸነፍ ወደ ተሰፋ ቡድን አወረዱት። በዓመቱ መጨረሻ ሽፈራው ተተካ። አንድሬ ቦሪ መምህር ነው፤ ዲሚትሪ በሀገሩ የመረብ ኳስ አሰልጣኝ ነው።ኬርቴስ በሀንጋሪ የሰርከስ አሰልጣኝ ነው ፤ሚሎዞቪች በአራተኛው ዓለም ዋንጫ ዮጎዝላቪያን በአሰልጣኝነት ይዞ የቀረበ ነው። የሰርከስ አሰልጣኙና በዓለም ዋንጫ ቡድን ይዞ የቀረበው አሰልጣኝ ኢትዮጵያን ሲያሰለጥን ግን ተመሳሳይ ውጤት ነው የገጠመው። እነዚህ አሰልጣኞች ሲፈራረቁ ሁሉም ዛሬም ድረስ ለውጥ አምጥተው የሀገራችን እግር ኳስ ከምራብና ሰሜን አፍሪካ ጋር ተወዳዳሪ ማድረግ አልቻሉም። ሁሉም የሚከተሉት ስልጠና ተመሳሳይ በመሆኑ በውጤትም ደካማና አንድ አይነት ናቸው። የመጀመሪያው አሰልጣኝ ጀርጅ ብራውን ሲቀጠር ያሳየውን ነገር ሁሉም ደግመውታል።

አሰልጣኝ ተቀያይሮ ለውጥ ካልተገኘ ስህተቱ ያለው ስልጠናው ላይ በመሆኑ ሰውየውን ከመቀየር ይልቅ ስልጠናውን መቀየር መፍትሄ መሆኑ ይታመናል። ይሄ ማለት ስልጠናው እኛ ተጫዋች ላይ መጻፍ አለበት። ያን ጊዜ የውጭ አሰልጣኝም አያስፈልግም ማለት ይሆናል። አንድ ቡድን የአጨዋወት ዘዴውን የሚዘረጋው ከሚይዘው ተጨዋች ተነስቶ ነው። የኛም ሀገር ስልጠና የኛን ተጫዋች መነሻ ባደረገበት መልኩ ሊሆን ይገባል። እስከዛሬ የሚሰጠው ስልጠና በባለጋራ በተለይ በምዕራብና ሰሜን አፍሪካ ጋር በንጽጽር ብልጫ እየተወሰደብን ነው ። ይሄን ለመቋቋም አዲስ የአጨዋወት ዘዴ መንደፍ የግድ ይላል። የአጨዋወት ዘዴውን ስንነድፍ ደግሞ ስልጠናውም ከዚህ አንጻር ሊቀረጽ ይገባል። ካለበለዚያ ውጤው በጠፋ ቁጥር ጀርመናዊ አባረን ሆላንዳዊ እንቀጥርና እሱንም አባረን እንግሊዛዊ እየቀጠርን መቀጠል እንዳይሆን ማሰብ ያስፈልጋል።

የፌዴሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች ቦታው ላይ ሲቀመጡ እንደተለመደው ልምድና ወረቀትን አይቶ አሰልጣኝ መቅጠር ብቻ መፍትሄ አይሆንም ። ወረቀት አይቶ መቅጠር እውቀት አይደለም። እውቅት የሚሆነው ችግሮችን አውቆ ለዚያ መፍትሄ የሚሰጥ አመራር ሲገኝ ብቻ ነው። ካለበለዚያ የአገሪቱ እግር ኳስ ካለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት በላይ እንደተጓዘው አመራር ይሄኛውም ምንም ነገር ሳያሳየን የስራ ጊዜውን አጠናቆ ይወርዳል።

እዚህ ጋር አንድ ምሳሌ ማንሳት አስፈላጊ ነው። በርቲ ፎክት የጀርመንን ብሄራዊ ቡድን በማሰልጠን በ1996 የአውሮፓ ቻምፒዮን አደረገው። በወቅቱ በዓለም ተቀባይነት ካላቸው አሰልጣኞች አንዱም ነበር። ፎክትን የኳታር እግር ኳስ ፌዴሬሽን በአሰልጣኝነት ቀጠረው። ግን ምንም ውጤት ማጣት አልቻለም። ፌዴሬሽኑ በተጫዋቾቹ ተበሳጭቶ «በዓለም አለ የተባለ አሰልጣኝ አመጣሁላችሁ፣ ከዚህ በላይ ምን ላድርግላችሁ» ብሎ የራሱን ድክመት በተጫዋቾቹ አሳበበ። በርቲ ፎክት ውጤት ያመጣው እነ ኪሊኒስማን ፤ ቢርሆፍና እነርሱን የመሳሰሉ ፈርጣማ ተጫዋች ይዞ ነው። ኳታር ውስጥ ያሉት ተጫዋቾች ያንን ሊተገብሩለት አልቻሉም። በርቲ ፎክትም የኳታርን ተጫዋቾች መነሻ ባላደረገ መልኩ ስላልሰራ ለውጥ አልተገኘም። የኳታርም ፌዴሬሽን ችግሩን ሳያውቅ እስካሁን በተለያየ ጊዜ ታዋቂ አሰልጣኞችን በመቅጠር እስካሁን ያለመፍትሄ እየተጓዘ ነው። ጀርመናዊ ፒተር ሽተንገር አይቮሪኮስትን ይዞ ኢትዮጵያን 6ለ1 አሸነፈ። ፒተር በአይቮሪኮስት ውጤቱ ጥሩ ስለነበረ የኛ ፌዴሬሽን ቀጠረው ። በ1968 ዓ.ም በአስረኛው አፍሪካ ዋንጫ በሜዳችን በጊኒ ተሸንፈን፣ በግብጽ ነጥብ ጥለን ከውድድር ልንወጣ «አይችልም» ተብሎ ተባረረ። ከ 11 ዓመት በኋላ ፒተር ሴኔጋልን ይዞ አዲስ አበባ መጣና በሜዳችን 2ለ1 አሸነፈን። ፌዴሬሽኑ ፒተርን ለመቅጠር እንደገና አነጋገረው። እሱ ግን ኮንትራት ስላለው ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ፒተር ችሎታ የለውም ወይስ ለስልጠናው (መነሻ) ነው ያጣው? አሁን ያለው የኛ ፌዴሬሽን ከፒተር መማር አለበት። ፒተር ለያዘው ስልጠና የምዕራብ አፍሪካ ቡድኖች ገላጭ ናቸው። ለስልጠናው መነሻ ከሌለን አሰልጣኝ መቅጠር ኪሳራና ጊዜ ማባከን ነው። በጣም ታዋቂ አሰልጣኝም ብናመጣም እሱ ለያዘው ነገር ሰው ከሌለን ዋጋ የለውም። ጀርመን በረጅም ርቀት ሩጫ ውጤት የሚያመጣ ቀርቶ ሚኒማ የሚያሟላ አትሌት የላቸውም። እኛ ውጤታማ ነን ። ግን ጀርመን በረጅም ርቀት በዓለም ውጤት ካላት ከኢትዮጵያ አሰልጣኝ አትቀጥርም። ምክንያቱም በረጅም ርቀት በተፈጥሮ ለዚህ የሚሆን አትሌት ስለሌላቸው አሰልጣኝ ምን ያደርግላቸዋል?። እኛ በእግር ኳስ ከጀርመን ብዙ ጊዜ አሰልጣኝ ቀጥረናል። ምክንያቱም ጀርመን በእግር ኳስ በዓለም ታላቅ ነች። ግን ጀርመኖች ውጤት ላመጡበት ስልጠና የኛ ተጫዋች መነሻ ሊሆኑ አልቻሉም።ያለመቻላቸው ያለፈው ጊዜ ውጤት ምስክር ነው።

የአፍሪካ አገራት የወዳጅነት ጨዋታዎች

ለካሜሩኑ የ2022 የአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ የማጣሪያ ጨዋታዎች ዳግም ከመጀመራቸው በፊት የአፍሪካ አገራት ለቅደመ ዝግጅት የሚረዳቸውን የወዳጅነት ጨዋታዎች ይፋ ማድረግ ጀምረዋል። ለካሜሩኑ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ድልድል ይረዳት ዘንድ በኢትዮጵያ ምድብ የምትገኘው ኮትዲቯር የወዳጅነት ጨዋታውን ጥቅምት 1 ከናይጀሪያ ጋር በአውሮፓ ምድር አስትሪያ እንደምታደርግ አሳውቃለች::

በ COVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት በአውሮፓ ምድር በአስትሪያ የሚደረገው የወዳጅነት ጨዋታ በናይጀሪያ ፣ በኮትዲቯርና በቱኒዚያ እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች የተዘጋጀና ከፍተኛ ግምት የተሰጠው የወዳጅነት ጨዋታ ነው። የቱኒዚያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እንዳስታወቀው፣ ብሔራዊ ቡድኑ ወደ አስትሪያ ከመጓዙ በፊት ከሱዳን ብሔራዊ ቡድን ጋር የመጀመሪያውን የሚሚቂያ ጨዋታ በቱኒዚያ በሐማዲ አግሬቢ አሊምፒክ ስታዲየም የሚከናወን ሲሆን ሁለተኛው ከናይጄሪያ ጋር አስትሪያ ላይ ጥቅምት 13 ለማካሄድ ተዘጋጅቷል ::

በተቃራኒው በአፍሪካ ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታዎች በቅርብ ርቀት የሚጠብቀው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እስካሁን አሰልጣኝ አልተቀጠረለትም:: በፌዴሬሽኑ በኩል ለገንዘብ ቁጠባ በሚል የአሰልጣኝ ቅጥር ሂደቱን ማዘግየቱንና የማጣሪያ ጨዋታው ሲቃረብ መቅጠሩን የመረጠ ይመስላል::

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በኩል የሚታሰብ ባይሆንም ከአፍሪካ አገራት ድንገት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ጋር የወዳጅነት ጨዋታ ለማድረግ የሚጠይቅ ቢኖር በፌዴሬሽኑ በኩል ምላሹ አሰልጣኝ ስለሌለን አንፈልግም ከማለት የሚቆጠብ እንደማይሆን መገመት አይከብድም ።